# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

81ኛ ዓመት ቁጥር 294 ሰኔ 24 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72

ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18

ይደውሉ

ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ


# የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት እንደገለጸው፡-

- መንግሥት በሩን ለሰላም ሲከፍት ከነሙሉ ዝግጁነቱና አቅሙ ጋር ነው
- በኦሮሚያ በንጹሃን ላይ ጭፍጨፋ የፈጸሙ ቡድኖች ተደምስሰዋል
- ሦስተኛው ዙር የህዳሴው ግድብ የውሃ ሙሌት በተያዘለት የጊዜ ገደብ ይከናወናል


ገጽ 4




ፎቶ - በገባቦ ገብሬ


ኦሮሚያን ይጎብኙ

የብዝሃ-ውበት ምድር!



Website: https://www.visitoromia.org
Facebook: https://www.facebook.com/visitoromia/
Instagram: https://instagram.com/VisitOromia
Twitter: https://twitter.com/VisitOromia
LinkedIn: https://linkedin.com/company/visitoromia
YouTube: https://YouTube.com/visitoromia
Pinterest: https://Pinterest.com/visit_oromia
Telegram: https://t.me/visit_oromia

ኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽን

www.visitoromia.org


## የነዳጅ እጥረቱ መንስኤ የኢኮኖሚ አሻጥር መሆኑን ባለሥልጣኑ አስታወቀ

ጌትነት ተስፋማርያም

አዲስ አበባ፡- በተለያዩ ከተሞች የታየው የነዳጅ እጥረት መንስኤው በነዳጅ ማመላለስ ሂደት ላይ በተከሰተ የኢኮኖሚ አሻጥር መሆኑን የነዳጅና ኢነርጂ ባለሥልጣን አስታወቀ።


የነዳጅ እጥረቱ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


## በኦሮሚያ ክልል በንጹሃን ዜጎች ላይ የተፈጸመው ጭፍጨፋ ምርመራ እየተካሄደበት መሆኑ ተገለጸ

ፀጋዬ ጥላሁን

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ወለጋ ዞን ጊምቢ ወረዳ፣ ቶሌ ቀበሌ አሸባሪው ሸኔ በንጹሃን ዜጎች ላይ የፈጸመው ጭፍጨፋ በፌዴራል ፖሊስ ምርመራ እየተካሄደበት መሆኑን የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት ገለጸ፡፡

የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት ፕሬስ ሴክሬታሪያት ቢልለኔ ስዩም ትናንት ለመገናኛ ብዙኃን በሰጡት መግለጫ፤ አሸባሪው ሸኔ በኦሮሚያ ክልል በሚንቀሳቀስባቸው አካባቢዎች የፌዴራልና የክልል የፀጥታ ኃይሎች የሚወስዱትን የሕግ የማስከበር እርምጃ መቋቋም ሲያቅተው በንጹሃን ዜጎች ላይ አሰቃቂ ግድያ ፈጽሟል፡፡

በቅርቡም በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ወለጋ ዞን ጊምቢ ወረዳ ቶሌ ቀበሌ አሸባሪው ሸኔ በንጹሃን ዜጎች ላይ የፈጸመውን ጭፍጨፋ ዝርዝር ሁኔታ በተመለከተ የፌዴራል ፖሊስ ምርመራ እያካሄደ ነው ያሉት ሴክሬታሪያቷ፤ የሽብር ቡድኑ ዓላማም በኦሮሞ እና አማራ ሕዝቦች መካከል ግጭት በመፍጠር በአገሪቱ አለመረጋጋት እንዲከሰት ማድረግ ነው ብለዋል፡፡

በአገሪቱ በተለያዩ አካባቢዎች በንጹሃን ዜጎች ላይ በአሸባሪዎች ጥምረት የተፈጸሙት አሰቃቂ የሰላማዊ ሰዎች ግድያዎች ዜጎችን ሆን ተብሎ በመንግሥት ላይ



ፎቶ - በፀሐይ ንጉሤ

ቢልለኔ ስዩም

ለማነሳሳት የተቀነባበሩ ድርጊቶች መሆናቸውንም ጠቁመዋል፡፡

አሸባሪው ሸኔ በፈጠረው የጸጥታ ስጋት ምክንያት ችግር ውስጥ ለወደቁ የሕብረተሰብ ክፍሎች አስፈላጊው እርዳታ እየተደረገ እንደሆነም በመግለጫቸው ጠቁመዋል፡፡

የጠላት ኃይሎች በተቀናጀ መልኩ በአገሪቱ አለመረጋጋት በመፍጠር ኢትዮጵያን ለመበተን እየሰሩ በመሆኑ መንግሥት የአገሪቱን የሰላምና ጸጥታ ጉዳይ አሁንም ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫ አድርጎ ለመቀጠል ቅድሚያ ሰጥቶ እየሰራ እንደሚገኝ ፕሬስ ሴክሬታሪያቷ ገልጸዋል።

በጦርነቱ በተጎዱ አካባቢዎች በተለይም ወደ ትግራይ በተሽከርካሪና በአየር ትራንስፖርት የሚደረገው የሰብአዊ እርዳታ ተጠናክሮ መቀጠሉን የጠቆሙት ፕሬስ ሴክሬታሪያቷ፤ በቅርቡም ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ፣ መድሃኒት፣ ነዳጅና ሌሎች በ488 ተሽካርከሪዎች ወደ ትግራይ መድረሳቸውን ተናግረዋል፡፡ ሆኖም ከተላኩት 488 ተሽከርካሪዎች መካከል 283ቱ ብቻ መመለሳቸውን አስረድተዋል፡፡

መንግሥት ለአሸባሪው ሕወሓት በተደጋጋሚ የሰላም እድሎችን መስጠቱን የጠቀሱት ፕሬስ ሴክሬታሪያቷ፤ በዚህም ብዙ ዋጋ መክፈሉን ተናግረዋል፡፡

መንግሥት በአፍሪካ ሕብረት መሪነት የሚደረገው የሰላም ውይይት ሕገ መንግሥቱን ባከበረ እና የአገሪቱን ብሄራዊ ጥቅም ባስከበረ መልኩ እንዲካሄድ መስፈርቶች ማስቀመጡ ይታወሳል ብለዋል፡፡





## በምክር ቤቱ ቢሮ ላይ ጉዳት ያደረሱ ሃይሉች ላይ ምርመራ እያካሄደ መሆኑን የፌዴራል ፖሊስ አስታወቀ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- በትናንትናው እለት በአዲስ አበባ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤት የቢሮ መስታወት በመሰባበር ጉዳት ያደረሱ ሃይሎች ላይ ምርመራ እያካሄደ መሆኑን ፌዴራል ፖሊስ አስታወቀ፡፡


በምክር ቤቱ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ

ADAMA STEEL FACTORY

ሚስማር ከ3 ቁጥር -15 ቁጥር





0940 505050/0940 606060/0940 909090/0940 808080/0920 656565

UNIC ETHIOPIA

ሕብረት ኢንሹራንስ አማ

THE UNITED INSURANCE COMPANY SC

Tomorrows Company Today'

ለህይወት

ለሁሉም የመድን ፍላጎትዎ

ህጋዊ ግዴታዎ

+251 111 26 34 34

united.insurance@unic-ethiopia.com

# የትምህርት ተቋማት በሳይንስና ቴክኖሎጂ የበለጸገ የሰው ሀብት ልማት ላይ በትኩረት ሊሰሩ እንደሚገባ ተገለጸ

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በሳይንስና ቴክኖሎጂ የበለጸገ የሰው ሀብት ልማት ማፍራት ላይ በትኩረት ሊሰሩ እንደሚገባ ተገለጸ። ቀጣሪ ድርጅቶችንና ተመራቂ ተማሪዎችን የሚያገናኝ አውደ ርዕይ በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ተከናውኗል።

የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ትናንት “ዩኒቨርሲቲ ለኢንዱስትሪ” በሚል መርህ አውደ ርዕይ ሲከፈት በትምህርት ሚኒስቴር የሳይንስና ምርምር ጉዳዮች ዳይሬክተር ጄነራል ዶክተር ሰለሞን ቢኖር እንደገለጹት፣ በሳይንስና በቴክኖሎጂ እውቀትና ክህሎት የዳበረ የሰው ሀብት ልማት መካሄድ ቅድሚያ ከተሰጣቸው የትኩረት መስኮች መካከል አንዱ ነው።

የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መደበኛና መደበኛ ባልሆኑ የትምህርት ፕሮግራሞች በመታገዝ ዘርፉን መምራት የሚችል ብቃት ያለው የሰው ኃይል ለማፍራትና የተመራማሪዎችን ቁጥር ማሳደግ የሚያስችሉ አገራዊ ፕሮግራሞች መተግበር ላይ ሚናቸው የጎላ ነው ብለዋል።

በአሁኑ ወቅት 57 የመንግሥትና የግል ዩኒቨርሲቲዎች ይገኛሉ ያሉት ዳይሬክተር ጀነራሉ፤ በየዓመቱ ከ200 ሺ በላይ ምሩቃን ቢወጡም ተገቢውን የስራ እድል የሚያገኙት ውስን መሆናቸውን ገልጸዋል።

የትምህርት ጥራት ጉድለት፣ የላላ የተቋማት ትስስር ፣ የተማሪዎች ተግባር ላይ የልምምድ ውስንነት፣ አማራጭ የስራ ዕድሎች አለመኖርና የአምራች ዘርፉ ስራ የመፍጠር አቅም ውስን መሆን ለስራ ዕድል መጥበብ ምክንያት መሆናቸውን በአብነት ጠቅሰዋል።

ትምህርት ሚኒስቴር ችግሩን ለመቅረፍም የተቋማት ትስስር ክፍተትን ለመቅረፍ የሚያግዝ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና የኢንዱስትሪ ትስስር የሕግ ማቀፍ ተዘጋጅቶ ወደ ስራ መግባቱን ገልጸዋል።

የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ኢንዱስትሪዎችንና ስራ ፈላጊ ምሩቃንን ለማገናኘት የሰራው ተግባር ግንባር ቀደም ሆኖ የሚጠቀስ ነው ያሉት ዶክተር ሰለሞን ፤ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በሳይንስና ቴክኖሎጂ የተቃኘ የሰው ሀብት ልማት ማፍራት ላይ በትኩረት ሊሰሩ ይገባል ብለዋል።

የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር ደረጀ እንግዳ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ በእውቀት፣ በክህሎት፣ በአመለካከትና ጊዜውን የጠበቀና አሁን ላሉብን ችግሮች መፍትሔ ሊሆኑ የሚችሉ ምሩቃንን ማፍራት ወሰኝ ነው። በሙያቸውና በዲስፕሊናቸው ብቁ እንዲሆኑ ዩኒቨርሲቲው ካሪኩለም በማዘጋጀት በመተግበር የተለያዩ ምዘናዎችን በመመዘን በቂና ብቁ መሆናቸውን በማረጋገጥ ከኢንዱስትሪዎች ጋር ለማስተሳሰር ሲሰራ ቆይቷል።

ተማሪዎች ከህሎት እንዲኖራቸው በክፍል ውስጥ ከሚማሩት ትምህርር በተጨማሪ በተጓዳኝ እንደየሙያቸው በተለያዩ ክበባት በችሎታቸው እንዲሳተፉ በማድረግ ሙያቸውን እንዲያዳብሩ ተደርጓል። ተመራቂዎች የኮሙኒኬሽን ክህሎታቸውን እንዲያጎለብቱና ብቁ እንዲሆኑ መደረጉን ተናግረዋል።

እንደ ዶክተር ደረጄ ገለጻ ፤ በዩኒቨርሲቲው በሙያ ማበልጸጊያ ማዕከሉ ውስጥ ራሳቸውን ለኢንዱስተሪው ዘርፍ እንዴት ማብቃትና ማዘጋጀት እንዳለባቸው የተለያዩ ሥልጠናዎች ለአንድ ሳምንት ሰጥቷል።

ተመራቂ ተማሪዎች በኢንዱስተሪው ዘርፍ ውስጥ ተፈላጊና ተመራጭ በመሆናቸው ከ50 በላይ ቀጣሪ ኢንዱስትሪዎች ተመራቂ ተማሪዎች የሰሯቸውን የፈጠራ ስራዎች በማየት እንዲቀጥሯቸው የሚያስችል የስራ አውደርዕይ በዩኒቨርሲቲው ለሁለተኛ ጊዜ መካሄዱን ተናግረዋል።

የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲው የኢንዱስ ትሪውን ፍላጎት መሰረት በማድረግ በተለያዩ የሳይንስ፣ ኢንጂነሪንግና ቴክኖሎጂ ዘርፎች የሰለጠነ የሰው ኃይል በማፍራት ለአገሪቱ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ዕድገት የበኩሉን አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ እንደሚገኝ ታውቋል።

# ኢንስቲትዩቱ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የጀመረውን ጥረት አጠናክሮ እንዲቀጥል ተጠየቀ

**ፋንታነሽ ክንዴ**



አቶ ኡመር ሁሴን

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት ባለፉት ዓመታት ግብርናውን ለማዘመንና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ሲያደርግ የነበረውን ጥረት አጠናክሮ እንዲቀጥል የግብርና ሚኒስትሩ አቶ ኡመር ሁሴን አሳሰቡ።

ሚኒስትሩ የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ ወደ ኢንስቲትዩት ማደጉ በተበሰረበትና እስካሁን የነበረውን የሥራ እንቅስቃሴ የሚዳስስ ውይይት ከባለድርሻ አካላት ጋር ትናንት ሲካሄድ እንደገለጹት፤ ኢንስቲትቱ ባለፉት ዓመታት ባከናወናቸው ሰፋፊ ሥራዎች በግብርናው ዘርፍ ያሉ ክፍተቶችን በመለየትና ክፍተቱን በመሙላት አመርቂ ውጤቶችን አስመዝግቧል። በቀጣይነትም ባለፉት ዓመታት ከነበረው ኃላፊነት ከፍ ያለና አሁን የደረስንበትን የእድገት ደረጃና የችግር ስፋት የሚመጥን ዝግጅት ሊኖረው ያስፈልጋል ብለዋል።

ምርትና ምርታማትን ለመጨመር በተሠራው ሥራ በተለይ በኩታ ገጠም እርሻ አሁን የተደረሰበት አራት ሚሊዮን ሄክታር የሚጠጋ ሥራ ማከናወን መቻሉን አስታውሰው፤ ይህን ሥራ አጠናክሮ በመቀጠል ከሰብልና ሆርቲካልቸር በተጨማሪ ወደ እንስሳት ሀብታችንም ጭምር በማስፋት ዘርን ለማዘመን ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያደርገውን እንቅስቃሴ አጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ጠቁመዋል።

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከኢንስቲትዩቱ ጋር በቅርበት እየሠራ መሆኑን የጠቀሱት ሚኒስትሩ፤ በዘርፉ የሚስተዋሉ ስብራቶችን ለመጠገንና ለማስተካከል ያለውን አቅም ለማጠናከርና በአግባቡ ለመጠቀም በትብበር እንደሚሠራ ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ማንደፍሮ ንጉሤ በበኩላቸው፤ ኢንስቲትዩቱ የግብርና ሥርዓቱን አንቀው የያዙት ችግሮችን በመለየት፣ መፍትሔ በማስቀመጥና የምርምር ሥራዎችን በማከናወን ዘርፉን ለማዘመን የሚያደርገውን ሥራ አጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

የዘርፉን ዋነኛ ፈጻሚ አካላት አቅም በመገንባት የግብርናውን ውጤታማነት ከፍ ለማድረግ በትኩረት ሲሠራ መቆየቱን አስታውሰው፤ ኢንስቲትዩቱ በትኩረት ከሚሠራቸው ሥራዎች አንዱ በሆነው የኩታ ገጠም እርሻ አርሶ አደሮች ወጥ የሆነ ምርጥ ዘርና ማዳበሪያ እንዲሁም ሌሎች ቴክኖሎጂዎችን እንዲጠቀሙ በማድረግ ከአምርቶ መመገብ ወደ አምርቶ ግብይት የሚሸጋገሩበትንና ምርታማነታቸውን ከፍ ለማድረግ የሚያደርገውን እንቅስቃሴ አጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

በዚህም እስካሁን ድረስ በኩታ ገጠም እርሻ ሦስት መቶ ወረዳዎችና ከሦስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን በላይ አርሶ አደሮችን ተደራሽ አድርጓል ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ በቀጣይነትም ተደራሽነቱን እያሰፋ በመሄድ ከሰብል በተጨማሪ ወደ እንስሳት ሀብት በተለይም ዶሮና ወተት ሀብት ላይ ትኩረት አድርጎ እንደሚሠራ ጠቁመዋል።

አሁን ላይ በተሰጠው ተጨማሪ ተልዕኮም የዘርፉ አጠቃላይ የአሠራር ሂደት የሚሻሻልበት ሁኔታ ላይ ያተኮረ ጥናትና ምርምር እንደሚያካሂድና በምርምር የተገኙ ውጤቶችም ተግባራዊ እንዲሆኑ አስፈላጊውን እገዛ ያደርጋል ያሉት ዶክተር ማንደፍሮ፤ ትራንስፎርሜሽንን እውን የሚያደርገው አርሶ አደሩ ስለሆነ ለአርሶ አደሮች የሚደረገውን እገዛ አጠናክረን እንቀጥላለን ብለዋል።

# ወደሰሜን ኢትዮጵያ የሚጓጓዝ የሕገወጥ ነዳጅ ፍሰት መኖሩን የነዳጅ አቅራቢ ድርጅት አስታወቀ

**ጌትነት ተስፋማርያም**



አቶ ታደሰ ኃይለማርያም

አዲስ አበባ፡- ወደሰሜን ኢትዮጵያ በተለይም ወደወልዲያና ቆቦ አካባቢ የሚጓጓዝ ከፍተኛ የሕገወጥ ነዳጅ ፍሰት መኖሩን የኢትዮጵያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅት አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ ታደሰ ኃይለማርያም በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ወደወልዲያና ቆቦና አካባቢዎች የሚጓጓዘው ሕገወጥ የነዳጅ ዝውውር መጠን እየጨመረ ስለመሆኑ በየጊዜው መረጃዎች ይደርሱናል፡፡

በሚደርሱን መረጃዎች መሰረት በበርሜል የታሸገ ሕገወጥ ነዳጅ ከኮምቦልቻ ጀምሮ በብዛት ተጭኖ እንደሚሄድ ማወቅ ተችሏል ያሉት ዋና ስራ አስፈጻሚው፤ የነዳጅ ፍሰቱ ወደሰሜን የመጨመሩ ምክንያት ምናልባትም ከአሸባሪው ሕወሓት ጋር ሊገናኝ ይችላል ብለዋል።

ሁል ጊዜም የተጨማሪ ገበያ ሲኖር ሕገወጥ የነዳጅ ፍሰቱ እንደሚጨምር ይታወቃል ያሉት አቶ ታደሰ፤ ወደትግራይ ክልል ነዳጅ በብዛት የማይገባበት ሁኔታ ስላለ በኮንትሮባንድ መልክ የማስተላለፍና ከፍተኛ ክፍያ የመቀበል ሁኔታ ሊኖር እንደሚችልም ጠቁመዋል፡፡

ይህ ሁኔታ ለነዳጅ ሕገወጥ ዝውውር ሳቢ ሁኔታ ስለሚፈጥር ከአማራ ክልል ቢሮዎችና ከሚመለከታቸው የፌዴራል ተቋማት ጋር የበለጠ ጉዳዩን ማየትና የመፍትሄ እርምጃ ማስቀመጥ እንደሚጠይቅ ገልጸዋል።

ከዚህ ቀደም ወደ ሞያሌና ያቤሎ መስመር የኬንያ ድንበር እንዲሁም በሶማሌ ክልል የድንበር አካባቢዎች ከፍተኛ የሕገወጥ ነዳጅ ፍሰት ይስተዋል እንደነበር ያስታወሱት ዋና ስራ አስፈጻሚው፤ ችግሩን በነዳጅ ኮታ አቅርቦት አሰራር ማስተካከል መቻሉን ገልጸዋል።

አሁን ላይ የሚታዩ ህገወጥ የነዳጅ ፍሰቶችንና ተያያዥ ችግሮችን ለመከላከል ከኮታ አቅርቦት ባለፈ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምንም ማሳደግ እንደሚገባ አቶ ታደሰ ተናግረዋል።

የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክ ሚኒስቴር በነዳጅ አመላላሽ ተሽከርካሪዎች ላይ በአስገዳጅነት የእንቅስቃሴ መቆጣጠሪያ (ጂፒኤስ) ቴክኖሎጂ እንዲገጠም የሚያስገድድ መመሪያ ተግባራዊ ለማድረግ ዝግጅት እያደረገ መሆኑን ጠቁመዋል።

ጂፒኤስ ቴክኖሎጂው ከተገጠመ የእያንዳንዱን ነዳጅ ጭነት መስመርና ያረፈበትን ቦታ መከታተል ስለሚቻል ሕገወጥ የነዳጅ ዝውውርን ለመቆጣጠር ይረዳል። በተለይም በውጭ ምንዛሬ ተገዝቶ የገባው ነዳጅ ተመልሶ ከአገር እንዳይወጣ ለመከላከል የቴክኖሎጂው አስፈላጊነት የጎላ ነው ብለዋል።

የኢትዮጵያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅት ኃላፊነቱ ነዳጅ ከውጭ አገራት ማስገባት ነው፤ በዚህም መሰረት በዚህ ዓመት 600 ሺህ ሜትሪክ ቶን ቤንዚን፣ 2 ነጥብ 8 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ናፍጣ እንዲሁም 400 ሺህ ሜትሪክ ቶን የአውሮፕላን ነዳጅ ቀርቧል።

ዋናው ትልቁ ስራችን ነዳጅ ማቅረብ ነው ያሉት አቶ ታደሰ በዚህ ረገድ አዲስ አበባ ውስጥ በተለያዩ ጊዜያት የነበረውን የነዳጅ አከፋፋዮች ችግር ለመቀነስ ከነዳጅ ዴፖ እንዲወጣ በማድረግ ችግሩን መቅረፍ ተችሏል ሲሉ አስረድተዋል።

የኢትዮጵያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅት በአማካይ የቀኑ ከሁለት ነጥብ ሰባት እስከ ሶስት ሚሊዮን ነዳጅ እያሰራጨ መሆኑን አስታውቋል።

በተለያዩ ጊዜያት ወልዲያ ከለተማ ላይ ሕገወጥ ነዳጅ የሚያጓጉዙ ሰዎች ተይዘዋል። ግንቦት ወር ጨመረሻ ላይ በአፋር ክልል በኩል በሕገወጥ መልኩ ወደ ትግራይ ክልል ሲጓጓዝ የነበረ ከአምስት ሺህ ሊትር በላይ የሚገመት ነዳጅ መያዙ የሚታወስ ነው። ችግሩ በዋግ ኽምራ ብሄረሰብ አስተዳደር፣ በሰሜን ጎንደርና በተለያዩ አካባቢዎችም ይስተዋላል።

ዜና

# የፈተና ኩረጃ ነውርነት የሁሉም አጀንዳ መሆን አለበት

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- ሌብነትን የሚጠየፍ ዜጋ ለማፍራት የፈተና ኩረጃ ነውርነት የሁሉም አጀንዳ መሆን እንዳለበት የአገር አቀፍ ፈተናዎች ኤጀንሲ ገለጸ። የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ በበኩሉ ኩረጃ የዘርፉ ትልቅ ጠንቅ መሆኑን አስታውቀዋል።

በአገር አቀፍ ፈተናዎች ኤጀንሲ የፈተና ዝግጅትና አስተዳደር ዳሬክተር አቶ አስማማው እስተዚያ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት ቃለምልልስ እንደገለጹት፤ ሌብነት የሚጠየፍ ዜጋ ለማፍራት ከጅምሩ የኩረጃ ችግርን መፍታት ወሳኝ ጉዳይ በመሆኑ ችግሩ ለአንድ ተቋም የሚተው ሳይሆን ሕዝባዊ ርብርብ ይፈልጋል።

በማሕበራዊ ሆነ በመደበኛ ሚዲያዎች አገርና ወገንን የማይጠቅሙ ነገሮች አጀንዳ ከማድረግ የአገሪቱ ችግር የሆነው ኩረጃን አጀንዳ ማድረግ አገራዊ ሃላፊነት መሆን አለበት ያሉት አቶ አስማማው፤ እስካሁን የፈተና አስጣጥን ውጤታማ ለማድረግ የተሰራው ሥራ አበረታች ቢሆንም አሁንም ብዙ ይቀራል ብለዋል።

እንደ አቶ አስማማው ገለጻ፤ በራስ መተማመን ለፈተና ተዘጋጅተው በመምጣት የሚያኮራ ውጤት የሚያመጡ ተማሪዎች እንዳሉ ሁሉ ለኩረጃ ራሳቸውን አዘጋጅተው የሚመጡ የተማሪዎች ቁጥር ቀላል አይደለም። ተማሪዎች ፈተናን ሰርተው ለማለፍ ያላቸው ፍላጎት እየቀነሰ መምጣቱ ደግሞ ለኩረጃ መፋፋም መንስኤ ሆኗል። በተለይ የአገር አቀፍና የክልላዊ ፈተናዎች የፈተና ስርቆት ለማስቀረት በቴክኖሎጂ እንዲታጀብ ሙከራ ቢደረግም ችግሩን ሙሉ በሙሉ ግን ለማቃለል አልተቻለም።

ፈተና ተማሪ ወሩን ወይም ዓመቱን ሙሉ የተማረውን ነገር ምን ያህል እንደ ተረዳ ለማወቅ እንደሚሰጥ የተናገሩት አቶ አስማማው፣ በፈተና ወቅት የሚኮርጁ ተማሪዎች መጀመሪያውኑ ትምህርቱን በአግባቡ እንደማይከታተሉ አጠያያቂ እንደማይሆንና በሌላው ጭንቅላት ፈተናውን በኩረጃ የተሻገረ ተማሪ ራሱንም፣ ቤተሰቡንም ብሎ አገሩን በአግባቡ ያገለግላል የሚል እምነት እንደሌላቸው ተናግረዋል።

የኩረጃ ተዋናዮዎች ፈርጀ ብዙ በመሆናቸው በትክክል ለይቶ ለማስቀመጥ አስቸጋሪ ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፣ መንስኤዎቹ ግን ለትምህርት ያለው ግንዛቤና ፍላጎት መቀነሱ፣ የመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ ውስንነት መኖርና የወላጆች ብሎም የማሕበረሰቡ ክትትል ማነስ መሆናቸውን ማስቀመጥ እንደሚቻል አስገንዝበዋል።

አንዳንድ የፖለቲካ ሰዎች ዘንድ ትምህርትን የፖለቲካ መሳሪያ የማድረግ ዝንባሌ በጥቅሉ የመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ ቀላል አለመሆኑን የጠቆሙት ዳይሬክተሩ፣ ተወደደም ተጠላም የነገው አገር ተረካቢ የአሁኑ ትውልድ በመሆኑ የአገሪቱ እጣ ፈንታ እንዲሰምር ትምህርቱን ከፖለቲካ በማላቀቅ በተለይ በእውቀቱና በክህሎቱ የታነጸ ዜጋ ለማፍራት ኩረጃን መከላከል የሁሉም ድርሻ መሆን ያስፈልጋል ብለዋል።

በተመሳሳይ መልኩ ኩረጃ የአገር ብሎም የከተማው መስተዳድር ችግር ነው ያሉት የአዲስ አበባ ከተማ ትምህርት ቢሮ የአጠቃላይ ፈተና ዝግጅትና አስተዳደር ምዘና ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ዲናኦል ጫላ ናቸው።

ፈተና ሲዘጋጅ በብዙ መልኩ በርካታ የአገር ሀብት የሚፈስበት በመሆኑ ኩረጃ ብክነትን ከማስከተሉም በላይ በጎበዝ ተማሪዎች ሥነልቦና ላይ የሚያሳድረው ጫና ከፍተኛ ነው ያሉት አቶ ዲናኦል፣ በተደረገው ክትትል በዋናነት ለኩረጃ ክፍተት የሚፈጥሩ ፈታኞች መሆናቸውን መግባባት ላይ ከተደረሰበት በኋላ ጥብቅ ቁጥጥር በመደረጉ በከተማው መሻሻል ታይቷል ብለዋል።

አቶ ዲናኦል፣ በከተማ አስተዳደሩ ኩረጃን ለመቅረፍ ውጤታማ ሥራ እየተሰራ መሆኑን ጠቅሰው፣ ችግሩን ሙሉ በሙሉ ለማስወገድ ግን ሕዝባዊ ተሳትፎን ማሳደግና የአመለካከት ለውጥ ማምጣት ያስፈልጋል ብለዋል።

# የሕግ ማስከበሩ ሥራ ለሽብር ተልዕኮ የሚንቀሳቀሱ አካላትን መልክ ያስያዘ እንደነበር ተገለጸ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል የተካሄደው የሕግ ማስከበሩ ሥራ ለሽብር ተልዕኮ የሚንቀሳቀሱ አካላትን መልክ ያስያዘ መሆኑን የአማራ ክልል መንግሥት ኮምዩኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ ኃላፊ አስታወቁ።

የቢሮ ኃላፊው አቶ ግዛቸው ሙሉነህ ወቅታዊ ጉዳዮችን አስመልክተው በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ ውስጣዊ አንድነትን ለማጠናከር እና የውጭ ጠላትን ለመመከት የሕግ ማስከበር ሥራ መጀመሩን አስታውሰው፤ የክልሉ የፀጥታ ምክር ቤት የሕግ ማስከበሩን ሂደትና ሌሎች ጉዳዮች ላይ ውይይት ማድረጉንም አስታውቀዋል።

የሕግ ማስከበሩ ስራ በሕዝብ ጥያቄ መሠረት መጀመሩን የጠቀሱት ሃላፊው፤ ሥራው ውጤት የታየበት መሆኑንም የፀጥታ ምክር ቤቱ መገምገሙንና ጉድለቶችንም መመልከቱንም ተናግረዋል።

አቶ ግዛቸው እንደጠቆሙት፤ በህግ ማስከበር ስራው በርካታ ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ሥር የዋሉ ሲሆን የፀጥታ ተቋማትም ራሳቸውን ያደራጁበት እንደሆነ ገልጸዋል።

ይህ ስራ ለክልሉ ስጋት ለሆኑ ጠላቶች ዝግጁነቱን ያሳየበት ነው ያሉት ኃላፊው ፤ለሽብር ተልዕኮ የሚንቀሳቀሱ አካላትን መልክ ያስያዘ መሆኑንም አመልክተው፤ ለጠላት ሲላላኩ የነበሩ የሽብር አካላት በቁጥጥር ሥር መዋላቸውንም ገልጸዋል፡፡

የሕግ ማስከበሩ ማዕከል ያደረጋቸው ጉዳዮች፤ በአሸባሪው ሕወሓት ከማረሚያ ቤቶች የወጡ ፍርደኞችን ወደ ሕግ ሥርዓቱ መመለስ፣ የከዳ የሠራዊት ሃይልና ያሸሸውን መሳሪያ መያዝ፣ ሕገወጥ የመሳሪያ አያያዝ እና አጠቃቀምን ሥርዓት ማስያዝን ጨምሮ ሥርዓት አልበኝነትን መግራት እንደነበር አውስተዋል።




አቶ ግዛቸው ሙሉነህ

በሽብርተኛው ሸኔ በንፁሀን ላይ ያደረሠው ጭፍጨፋ የሚወገዝ እና በሁለንተናዊ አንድነት እና የሕግ ማስከበር ስራ ምንጩን ማድረቅ እንደሚገባ የገለጹት ሃላፊው፤ ይህንን ተከትሎ ሕዝብ በቁጭት የሚያደርገውን የሽብር ተቃውሞ ለዓላማቸው ማስፈፀሚያ ለሚያደርጉ አካላት በሚያመች መልኩ እንዳይሆን ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚያስፈልግም አሳስበዋል።

ክልሉን ለጥቃት እና ሽብር የተመቸ ለማድረግ የሚሠሩ አካላት በርካታ መሆናቸውን የገለፁት ሃላፊው ሕብረተሠቡ በሠከነ መልኩ አንድነቱን መጠበቅ ላይ ትኩረት እንዲያደርግ ማሳሰባቸውን የአሚኮና የኢቢሲ ዘገባ አመልክቷል።



ፎቶ - ፀሐይ ንጉሤ

# ጭቆናና ኢፍትሃዊነትን የታገለው የጥበብ አርበኛ ሲታወስ

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

የሰው ልጅ እድሜ አጭር ቢሆንም መልካም ይሁንም መጥፎው ሥራዉ ለትውልድ የሚተላለፍ መሆኑ የተፈጥሮ ሕግጋትን ሚስጥራዊ ያደርጋል። የተፈጥሮን ሕግ በመጣስ ለዘላለም መኖር እንደማይቻል የተገነዘቡ አንዳንድ የዓለማችን ሰዎች ባላቸው አጭር የምድር ላይ ቆይታ ውስጥ በሥራቸው ዘላለማዊ አሻራ አስቀምጠው አልፈዋል። ይህ ደግሞ “ኖረ ሞተ” ብቻ ከመባል እጅጉ መታደል ነው ይላሉ።

ከዚህ አንጻር በለጋ እድሜው ከጥበቡ ፍቅር ባሻገር በውስጡ ባደረው የሕዝቦች እኩልነትና ፍትሃዊነት ከብዙ ውጣውረዶችና መስዋእትነት በኋላ የብዙሃኑን ሕዝብ ቀልብ የገዛው አርቲስት ሀጫሉ ሁንዴሳን ማንሳት ተገቢ ነው።

አርቲስቱ የሕወሓት መራሹ መንግሥት ኢፍትሃዊነትና አምባገነንነት ለአንዲት ነፍሱ ሳይሰስት በጀግንነት በመጋፈጡ ምክንያት ከትምህርት ገበታና ማሕበራዊ ኑሮ በመታገድ ለዓመታት በአምቦ እስር ቤት ለማሳለፍ ተገዷል። ሀጫሉ በእስር ቤቱ የነጻነት ታጋዮች ላይ የሚደርሰውን በደልና እንግልት በሙዚቃው ያስቃኘ ባለሙያ ነው።

ሀጫሉ ለጆሮ የሚጥሙ ጥልቅ የማሕበራዊ፣ የኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መልእክት ያላቸውን ዜማዎች በአፋን ኦሮሞና በአማርኛ ለሕዝብ ጆሮ በማድረስ ዝናን ያተረፈ አርቲስት ነው።

አርቲስቱ በሕወሓት መራሹ መንግሥት ማብቂያ አካባቢ የአገዛዝ ዘመኑን ለማርዘም እየተፍጨረጨረ ያለውን መንግሥት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አሸቀንጥሮ ለመጣል በተለይ በሚሊንየም አዳራሽ ከሱማሌ ክልል ለተፈናቀሉ ዜጎች በተዘጋጀው የእርዳታ ማሰባሰቢያ ፕሮግራም ላይ አንዲት ነፍሱን አስይዞ ከጨካኞቹ የሕወሓት ባለሥልጣናት ጋር አንገት ለአንገት መተናነቁ መቼም የማይረሳ ጀብድ ነው።

ለዚህም ሲባል በአንድ በኩል የአርቲስቱን ሌጋሲ ለማስቀል በሌላ በኩል ደግሞ የኦሮሞ አርቲስቶችን ለማበረታታት ታስቦ ሀጫሉ ሁንዴሳ ፋውንዴሽን ተቋቁሟል። በዘንድሮ ዓመትም ለኦሮሞ አርት እድገት የላቀ አስተዋጽኦ ላበረከቱት የኪነጥበብ ባሙያዎች እውቅናና ሽልማት በአርቲስቱ ስም ተበርክቶላቸዋል።

በዚሁ ሥነሥርዓት ላይ የአርቲስቱ ባለቤት ወይዘሮ ፋንቱ ደምሰው እንደገለጸችው፤ ሀጫሉ በተፈጥሮው ማስመሰል የማይችል በየትኛውም የሰው ዘር ላይ ጭቆናና ኢፍትሃዊት እንዳይደረግ አጥብቆ የሚጠላና በቁርጠኝነት የሚታገል ሰው ነበር።

ሀጫሉ በእድሜ ታናሽ ቢሆንም በአርአያነቱ የሁሉንም በተለይ የወጣቱ ትውልድ ልብ ውስጥ እንደ ነገሰና ሌሎችንም ወደ አርቱ እንደሳበ አያጠያይቅም ብላለች።

በምርጥ ነጠላ ዘፈንና በምርጥ ዜማ የ300 ሺህ ብር ተሸላሚ የሆነው አርቲስት ዮሰን ጌታሁን በዚሁ ጊዜ በሀጫሉ ፍቅር ወደ ሙዚቃው መምጣቱን ጠቁሞ፤ ሀጫሉ አስተማሪው መሆኑን መስክሯል።

ዳሩ ግን ሀጫሉ በሕይወት ባይኖርም በሥራዎቹ ከመቃብር በላይ በመሆኑ ሁሉም እንደ ሀጫሉ በተሰማራው የሙያ መስክ ውጤታማ በመሆን ለእኩልነት፣ ለወንድማማችነትና ለፍትህ ጥብቅና መቆም ይጠበቅበታል ብሏል።

# የቱሪዝም ዘርፉን ለማሳደግ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ፖሊሲ ነድፎ መንቀሳቀስ እንደሚገባ ተጠቆመ

**አብዱረዛቅ መሐመድ**

ሰመራ፡- ለሀገሪቱ የቱሪዝም ዘርፍ እድገት ከቱሪዝም ፖሊሲ ጎን ለጎን ወቅታዊና ተለዋዋጭ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ ያስገባ ጠንካራ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ፖሊሲና ስትራቴጂ ነድፎ መንቀሳቀስ እንደሚገባ የውጭ ግንኙነት ኢንስቲትዩት አስገነዘበ።

የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ደሳለኝ አምባው ትናንት በሰመራ ከተማ በተካሄደው የፖሊሲ የውይይት መድረክ እንደተናገሩት፤ ለቱሪዝም ዘርፉ እድገት የሀገር ውስጥ ጎብኚውን ቁጥር ማሳደግ ትኩረት ቢያሻውም በተለይም ሀገሪቷ በየጊዜው የሚፈትናትን የውጭ ምንዛሪ እጥረት ለመቅረፍ የውጭ ሀገር ጎብኚዎችን ቁጥር ከማሳደግ አንጻር በርካታ ሥራዎች መሠራት አለባቸው።

በተለምዶ “ጭስ አልባ ኢንዱስትሪ” በመባል የሚጠራው የቱሪዝም ኢንዱስትሪ ለብዙ ሀገራት አማራጭ የኢኮኖሚ መሠረት ሆኖ ያገለግላል ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ኢትዮጵያ ካላት እምቅ የቱሪዝም ሀብት አንጻር ሲመዘን በተለያዩ ምክንያቶች ከዘርፉ መጠቀም ባለባት ልክ መጠቀም አልቻለችም ሲሉ ገልጸዋል።

እንደሀገር ያሉንን ሰው ሠራሽና ተፈጥሯዊ ሀብቶቻችንን በአግባቡ ከተጠቀምን እንደብዙዎቹ ሀገራት ሁሉ በሥራ ፈጠራ፣ የውጭ ምንዛሪን በማስገኘትና የሀገራዊ ምርት እድገትን በማረጋገጥ የኢኮኖሚ መሠረት መሆን ይችላል” ብለዋል።

አክለውም፣ ይህ ህልማችንና የዘወትር ቁጭታችን እውን እንዲሆን ሌሎች መሠራት ያለባቸው ሥራዎች እንዳሉ ሆነው በዋናነት የጠራ የዘርፉ ፖሊሲና ተያያዥ የማስፈጸሚያ ስልቶች ወይም ስትራቴጂዎች የአንበሳውን ድርሻ እንደሚይዙም አብራርተዋል።

የሀገሪቱ የቱሪዝም ዘርፍ እንዲያብብና ለኢኮኖሚ እድገት ተገቢውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት የሁሉም ባለድርሻ አካላትን ቅንጅታዊ አሠራር እንደሚጠይቅ ጠቅሰው፤ አግባብነት ያለው ፖሊሲና ስትራቴጂ መንደፍና ማስፈጸም፣ ሰላምና ጸጥታን ማስፈን፣ የመሰረተ ልማት እንዲሁም አገልግሎት ዘርፉን ማዘመንና ለጎብኚዎች ምቹ ማድረግ በዋናነት ከመንግሥት የሚጠበቅ ቢሆንም በዚህ ረገድ የግሉ ዘርፍም ጉልህ ሚና እንደሚጫወት ጠቁመዋል።

በተጨማሪም፣ ተመራማሪዎች በቱሪዝም ዲፕሎማሲና የቱሪዝም ዘርፉን ማሳደግ በሚቻልባቸው ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ጥልቅ ጥናት ከማድረግም ባለፈ የምርምር ውጤቶቻቸው ለፖሊሲ እና ትግበራ እንዲያግዙ ተደራሽ ማድረግ አለባቸው።

የፕሮሞሽን ባለሙያዎች፣ የጥበብ ሰዎች፣ የሀገር ሽማግሌዎች እና የባሕል አምባሳደሮች ድርሻም ቀላል የሚባል አይደለም ሲሉ አስረድተዋል።

በውጭ ግንኙነት ኢንስቲትዩት በተዘጋጀው በዚህ የውይይት መድረክ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ለቱሪዝም ዘርፍ እድገት ያለውን ሚና እንዲሁም የኢትዮጵያ የቱሪዝም ዲፕሎማሲ ስትራቴጂያዊ አቅጣጫዎች፣ ትግበራ እና ተግዳሮቶች ላይ ያተኮሩ ጥናታዊ ጽሁፎች በዘርፉ ምሁራን ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸዋል።

በውይይት መድረኩ የፌዴራልና የክልል የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች፣ የዩኒቨርሲቲ መምህራንና ተመራማሪዎች፣ የቱሪዝም ዘርፍ ባለሙያዎችና ሌሎችም ተጋባዥ እንግዶች መታደማቸውን ለማወቅ ተችሏል።

ዜና

# የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት እንደገለጸው፡-

- መንግሥት በሩን ለሰላም ሲከፍት ከነሙሉ ዝግጁነቱና አቅሙ ጋር ነው
- በኦሮሚያ በንጹሃን ላይ ጭፍጨፋ የፈጸሙ ቡድኖች ተደምስሰዋል
- ሦስተኛው ዙር የህዳሴው ግድብ የውሃ ሙሌት በተያዘለት የጊዜ ገደብ ይከናወናል

**ሞገስ ጸጋዬ**



አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ መንግሥት በሩን ለሰላም ሲከፍት ከነሙሉ ዝግጁነቱ፣ አቅሙና ብቃቱ ጋር መሆኑን የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት አስታወቀ። በኦሮሚያ ክልል በንፁሃን ዜጎች ላይ ጭፍጨፋ የፈፀሙ የሸብር ቡድኖች ላይ በተቀናጀ የፀጥታ አካላት በተወሰደ እርምጃ መደምሰሳቸውም ተገልጿል።

በተያያዘ ዜና ሦስተኛው ዙር የህዳሴው ግድብ የውሃ ሙሌት ያለአንዳች ችግር በተያዘለት የጊዜ ገደብ እንደሚከናወንም ተገልጿል።

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዶክተር ለገሰ ቱሉ በትናንትናው ዕለት በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ የኢትዮጵያ መንግሥት በሩን ለሰላም ሲከፍት ከነሙሉ ዝግጁነቱ፣ አቅሙና ብቃቱ ነው።

የሸብር ቡድኑ ሰላምን እንደ ማዘናጊያ እንደሚጠቀምበት ግልጽ ነው ያሉት ዶክተር ለገሰ፤ ነገር ግን ሰላም የሚጠቅመው የትግራይን ሕዝብና ራሱን አሸባሪውን ሃይል በመሆኑ ለዳግም ጦርነት ከመዘጋጀት ወጥቶ የሰላም እድሉን መጠቀም መቻል አለበት ብለዋል። የጦርነት ጉሰማዎች እንደማያዋጡ ከዚህ በፊት በነበረው ጦርነት መረጋገጡንም አስገንዝበዋል።

መንግሥት በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ያለው ጦርነት በሰላማዊ ሁኔታ እንዲቋጭ ዝግጁ መሆኑን በተደጋጋሚ ገልጿል ያሉት ሚኒስትሩ፤ መንግሥት ለሰላም በሩ ክፍት ነው፤ ያሉ ችግሮችን በሰላምና በእርቅ እፈታለው ካለ አካል ጋር ለመወያየት ዝግጁ ነው ብለዋል።

እንደ ዶክተር ለገሰ ገለጻ፤ መንግሥት ሰላም ለማውረድ ዝግጁ ሲሆን የሰላም ሁኔታ በአንድ ወገን ብቻ ይወሰናል ብሎ በማሰብ ሳይሆን መንግሥት ለሰላም ዝግጁ በመሆኑ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላም በተረጋገጠለት መጠን ብልጽግናው የሚረጋገጥለት በመሆኑ መንግሥት ለሰላም ቅድሚያ ይሰጣል። እንዲሁም የተረጋጋ የፖለቲካ ሥርዓትን ለመፍጠር በመንግሥት በኩል ለሰላም ሙሉ ለሙሉ ዝግጁ ነው። ይህ የሰላም ፍላጎት በሌላኛው ወገን የሚኖረው ተቀባይነት ግን በቀጣይ የሚታይ ነው ብለዋል።

በመላ ሀገሪቱ ለተፈናቀሉ ዜጎች የሚደረገው የሰብአዊ እርዳታ ተጠናክሮ ቀጥሏል ያሉት ዶክተር ለገሰ፤ በትግራይ ክልል በአስቸጋሪ ሁኔታ ያሉ ዜጎችን ለመታደግ ከተለያዩ ለጋሽ ድርጅቶች ጋር በመሆን በጥሬ ገንዘብ ከ2 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር በላይ እርዳታ ተደርጓል ብለዋል።

እንዲሁም 234 ነጥብ 37 ሜትሪክ ቶን መድኃኒት፣ 155 ሺህ 500 ቶን ምግብ ነክ፣ 18 ሺህ 658 ሜትሪክ ቶን ምግብ ነክ ያልሆኑ ድጋፎች፣ 987 ሺህ 137 ሊትር ነዳጅ በአጠቃላይ 5 ነጥብ 2 ሚሊዮን ለሚሆኑ የትግራይ ነዋሪዎች የሰብአዊ እርዳታ ቀርቧል ብለዋል።

በሕግ ማስከበር በተወሰደው እርምጃው መሰረት በአማራ፣ በኦሮሚያና በጋምቤላ ክልሎች ውጤት ተገኝቷል ያሉት ሚኒስትሩ፤ የሸብር ቡድኖች አለን ለማለት ከየተበታተኑበት ተሰባስበው በንጹኃን ዜጎቻችን ላይ በኦሮሚያና በጋምቤላ ክልሎች እጅግ ዘግናኝ ተግባር ፈጽመዋል ብለዋል።

በቶሌ ቀበሌ የፈጸሙት ድርጊት ተጨባጭ የሸብር ስራቸውን በገሀድ ያሳዩበት ነው ያሉት ዶክተር ለገሰ፤ ዋና ዓላማቸው በሕብረተሰቡ መካከል ግጭት በመፍጠር መረጋጋት እንዳይፈጠር በማድረግ ከቻሉ ሀገርን ማፍረስ እንደሆነም ጠቁመዋል። በንጹሃን ላይ የተከሰተውን ድርጊት ተከትሎ መንግሥት ችግሩ በተፈጸመባቸው አካባቢዎች አፋጣኝ እርምጃ መውሰዱንም ተናግረዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ በኦሮሚያ ክልል በንጹሃን ላይ ጭፍጨፋ ያካሄዱ የሸብር ቡድኖች በተቀናጀ የጸጥታ አካላት በተወሰደ እርምጃ አብዛኞቹን የሸብር ቡድን ተሳታፊዎች መደምሰስ ተችሏል፤ ወደ ጫካ የተበታተኑ የሸብር ቡድኑ አባላትም በጸጥታ ኃይሎችና በሕብረተሰቡ ትብብር እየታደኑ ይገኛሉ።

በአካባቢው ጉዳት የደረሰባቸውን ቤተሰቦች የማረጋጋትና ከአካባቢው የተፈናቀሉ ዜጎችን ወደ መንደራቸው እንዲመለሱ፣ የቆሰሉ እንዲታከሙ፣ ንብረታቸው የወደመባቸው የዕለት ደራሽ ምግብና ቁሳቁስ እርዳታ እንዲያገኙ መደረጉንም ሚኒስትሩ አስረድተዋል። በጫካ በመደበቅ በሰላማዊ ዜጎች ላይ ዳግም ጉዳት እንዳያደርሱም ሕዝቡ ተደራጅቶ እንዲንቀሳቀስ ይደረጋል ብለዋል።

በተያያዘ ዜና ሦስተኛው ዙር የህዳሴው ግድብ የውሃ ሙሌት ያለአንዳች ችግር በተያዘለት የጊዜ ገደብ እንደሚከናወንም ሚኒስትሩ ገልጸዋል።

ይህ እቅድ እውን እንዳይሆን ከመላው ሕዝብ አንድ ሆኖ መቆም ይጠበቃል ያሉት ዶክተር ለገሰ፤ ሴረኞች በኃይማኖት፣ በብሔር፣ በአካባቢና በተለያዩ መልኮች የሚፈጠሩ ግጭቶችና በድንበር አካባቢ የሚደረጉ ጫናዎች ሶስተኛውን ዙር የውሃ ሙሌት በተያዘለት የጊዜ ገደብ እንዳይሞላ ለማዘናጋት ነው ብለዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ ሶስተኛው ዙር የህዳሴ ግድብ በተያዘለት የጊዜ ገደብ እንዳይሞላ በጋውን ጨምሮ የተለያዩ እንቅፋቶች ሲፈጠሩ ቆይተዋል። አሁንም በተለያየ መልክ በሕብረተሰቡ ውስጥ የተለያዩ አጀንዳዎችን በመፍጠር ሕብረተሰቡ እርስ በርሱ እንዳይተማመንና እርስ በርስ ግጭት ውስጥ እንዲገባ በማድረግ ሰላምና መረጋጋት እንዳይኖር እየሰሩ ነው።

በኢትዮጵያ ውስጥ በየአካባቢው ሁከትና ብጥብጥ በመፍጠር መንግሥትን ከያዘው እቅድ ለማሰናከልና ትኩረቱን በማስቀየር ከሕዳሴው ግድብ የውሃ ሙሌት ጉዳይ ለማዘናጋት እቅዶች አሉ ያሉት ሚኒስትሩ፤ ይሁን እንጂ ይህ የሚሳካ ጉዳይ አለመሆኑን ገልጸዋል።

እንደ ዶክተር ለገሰ ገለጻ፤ መጪው ጊዜ ክረምት መሆኑ ብቻ ሳይሆን ወሳኝ የሆነውን የሶስተኛው ዙር የሕዳሴውን ግድብ የምንሞላበትና ተጨማሪ ኃይል ማመንጨት የምንጀምርበት ወቅት ነው። ይህን አኩሪ ታሪካዊ አሻራ እንዳናሳካ የሚፈልጉ ኃይሎች ከውስጥ ባንዳዎች ጋር ጠንካራ ትስስር የፈጠሩ መሆኑን ሕዝቡ ተገንዝቦ አካባቢውን መጠበቅ፣ በምርት ማምረት ተግባር ላይ መሰማራት እና ሕብረብሔራዊ አንድነቱን ጠብቆ በመሄድ የሕዳሴውን የውሃ ሙሌት ለማሳካት መረባረብ አለበት።

## የነዳጅ እጥረቱ መንስኤ የኢኮኖሚ አሻጥር ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ከጂቡቲ ተነስተው አዲስ አበባና የተለያዩ ዋና ከተሞች መድረስ የነበረባቸው 200 የነዳጅ ጫኝ ቦቴዎች በተለያዩ ከተሞች በሚገኙ መንደሮች ውስጥ ተደብቀው መገኘታቸው ተገልጿል።

የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ ሰህረላ አብዱላሂ ትናንትና በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ ከቀናት በኋላ የነዳጅ ዋጋ ይጨምራል በሚል እሳቤ ከጂቡቲ የተነሱ የነዳጅ አመላላሽ ቦቴዎች በሕገወጥ መንገድ በየመንገዱ በመቆማቸው የነዳጅ እጥረት ተከስቷል። ይህን የኢኮኖሚ አሻጥር ለመከላከልም መጠነ ሰፊ ቁጥጥር እየተከናወነ ይገኛል።

ችግሩን ለመከላከል በተደረገው የቁጥጥር ስራ አዲስ አበባና ሌሎች ዋና ዋና ከተሞች ላይ መድረስ የነበረባቸው ቦቴዎች በየመንደሩ ተደብቀው ተይዘዋል ያሉት ዋና ዳይሬክተሯ፤ ችግሩ ከጂቡቲ ወደ አዲስ አበባ በሚወስደው መንገድ ላይ በብዛት እንደታየ ገልጸዋል።

በተለይ አፋር ላይ በሕገወጥ መንገድ ነዳጅ ይዘው የቆሙ 15 ቦቴዎች መገኘታቸውን አስታውሰው፤ ከጸጥታ ኃይሎች ጋር በትብብር በተከናወነ የቁጥጥር ስራ ከጂቡቲ ተነስተው ወደ ማደያዎቻቸው ሳይደርሱ በሰዋራ ስፍራ የቆሙ የነዳጅ ቦቴዎችን በመተሃራ ፣ በምስራቅ ሸዋ ዞን፣ በሞጆ፣ በአዳማ ከተሞች በተለያዩ ስፍራዎች ላይ መያዛቸውን አስታውቀዋል።

በመተሃራና አዳማ ከተሞች ከሰዋራ ስፍራዎች በተጨማሪ በሆቴሎችና በፋብሪካ ጊቢዎች እንዲሁም በትምህርት ቤቶች አካባቢ ጭምር ተደብቀው የተገኙ ነዳጅ ማመላለሻዎች መኖራቸውን ጠቁመዋል።

እንደ ዋና ዳይሬክተሯ ገለጻ፤ እስከትላንት ድረስ በአጠቃላይ በሕገወጥ መንገድ ያለስራ ቆመው የተገኙ ነዳጅ የጫኑ ቦቴዎች ቁጥር 200 ደርሰዋል። የተያዙት ተሽከርካሪዎችም በአፋጣኝ የጫኑትን ነዳጅ ወደየማደያዎቻቸው አድርሰው ሪፖርት እንዲያደርጉ ጥብቅ መመሪያ ተላልፏል።

የነዳጅ አቅርቦትና የማደያዎችን አገልግሎት በተመለከተ ችግሩን ለመከላከል በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሚመራ የጋራ ግብረሃይል መቋቋሙንም ወይዘሮ ሰዓረላ ገልጸዋል።

የጋራ ግብረ ሃይሉም የተለያዩ የጸጥታ አካላትንና የንግድ ቢሮዎችን እንዲሁም የነዳጅና ኢነርጂ ባለሥልጣንና ሌሎች የሚመለከታቸውን አካላት ያካተተ ነው ብለዋል።

ግብረ ኃይሉም የነዳጅ አሻጥር የሚፈጽሙትን ኩባንያዎች በመለየት ጥብቅ እርምጃ ለመውሰድ ዝግጅት አድርጓል ያሉት ወይዘሮ ሰህረላ፤ ችግሩ የተገኘባቸውን ከነዳጅ እደላ ኮታ ለተወሰነ ጊዜ እስከማገድ አንስቶ ንግድ ፈቃዳቸውን እስከመሰረዝ የሚደርስ እርምጃ እንደሚወሰድባቸውም ጠቁመዋል።

ሆን ተብሎ የተፈጸመው የኢኮኖሚ አሻጥር ተባባሪ የሆኑ አካላትን የመለየት ስራም እየተከናወነ ይገኛል ሲሉ አስረድተዋል።

የመንግሥት የነዳጅ አቅርቦቱ ባልተቋረጠበት ሁኔታ በሰው ሰራሽ መንገድ የነዳጅ እጥረት የሚፈጽሙ ማደያዎች ላይም የሚከናወነው ቁጥጥር ከወትሮው በተለየ ጠንካራ እንደሚሆን ገልጸው፤ ሕብረተሰቡም በየአካባቢው ተደብቀው የቆሙ የነዳጅ ቦቴዎችን ሲያገኝና የነዳጅ አቅርቦት ላይ የሚፈጸሙ አሻጥሮችን ሲያጋጥሙት ለሚመለከተው የጸጥታ አካል ሪፖርት እንዲያደርግ ጥሪ አቅርበዋል።

በነዳጅ አቅራቢ ድርጅት የአቅርቦትና ሽያጭ ኃላፊ አቶ አባይነህ አወልና የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ መስፍን አሰፋ በበኩላቸው፤ አንድ የነዳጅ ጫኝ ቦቴ ከጂቡቲ ተነስቶ አዲስ አበባ ለመድረስ ከሶስት እስከ አራት ቀን እንደሚፈጅበት ጠቁመው፤ በየመንደሩ ተደብቀው የተገኙት ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ግን ከጂቡቲ ከተነሱ ከአራት ቀን በላይ ያስቆጠሩ መሆናቸውን ገልጸዋል።

እንደ ሃላፊዎቹ ገለጻ፤ ከነዳጅ አመላላሽ ቦቴዎች በተጨማሪ በማደያዎች ያለውን የአገልግሎት ችግር ለመቅረፍ የተጠናከረ ቁጥጥር ይደረጋል።

የነዳጅ ድጎማ አገልግሎት ከሐምሌ ወር አንስቶ ተግባራዊ እንደሚደረግ መንግሥት ማሳወቁ የሚታወስ ነው።

## በምክር ቤቱ ቢሮ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ፌዴራል ፖሊስ ባወጣው መግለጫ ጽንፈኛ ኃይሎች ከውስጥና ከውጭ ጠላቶቻችን ጋር በመቀናጀት የሀገሪቱን ሰላምና ደህንነት ለማወክ እየሰሩ መሆኑን ፖሊስ ባገኛቸው መረጃዎች ማረጋገጡን አስታውቋል።

አለመግባባቶችን ሰበብ በማድረግ ጽንፈኛ ኃይሎች ከውስጥና ከውጭ ጠላቶቻችን ጋር በመቀናጀት የሀገራችንን ሰላምና ደህንነት ለማወክ እየሰሩ መሆኑን ፖሊስ ባገኛቸው መረጃዎች አረጋግጧል ብሏል መግለጫው።

በመግለጫው እንደተመላከተው፤ በትናትናው እለት የተደራጁ ኃይሎች የአዲስ አበባ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤት ቢሮን መስታወት በመሰባበር መጠነኛ ጉዳት አድርሰዋል።

ፖሊስ እነዚህን ኃይሎች በቁጥጥር ስር አውሎ በሕግ አግባብ ተጠያቂ እንዲሆኑ ምርመራ እያጣራባቸው መሆኑን ይገልፃል።

ከዚህ በተጨማሪ ጽንፈኛ ኃይሎች ከውጭ ጠላቶቻችን ጋር ተቀናጅተው የሀገራችንን ጸጥታ ለማደፍረስ የተለያዩ መሣሪያዎችን ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ጥረት እያደረጉ እንደሆነ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

ስለሆነም መላው የሀገራችን ሙስሊም ሕብረተሰብ ይህንን ተገንዝቦ የሀገሩንና የሃይማኖቱን ሰላምና ደህንነት እንዳይደፈርስ የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ እያሳሰበን፣ ፖሊስ ከድርጊታቸው በማይቆጠቡት ላይ ጥብቅ ሕጋዊ እርምጃ የሚወስድ መሆኑን ያሳውቃል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የኢትዮ-ሱዳን ህዝቦች ወንድማማችነት ካጋጠማቸው ወቅታዊ ችግር በላይ ነው!

ኢትዮጵያና ሱዳን የረጅም ዘመን የጉርብትና ታሪክ ያላቸው፤ የአንድ ወንዝ ውሃ የሚጠጡ፤ የመጪው ዘመን ዕጣ ፈንታቸውም የጋራ የሆነ ወንድማማች ህዝቦች ናቸው። እንደ ሕዝብ ብዛት ያላቸውን ማህበራዊ፣ ሀይማኖታዊ እና ባህላዊ እሴቶችን የሚጋሩ፤ አብሮ በሰላም በመኖርም ረጅም ዘመን ያስቆጠሩ ናቸው።

የአገራቱ ሕዝቦች ዘመናት ባስቆጠረው አብሮ የመኖር ታሪካቸው መተማመን፤ ከዚህ የሚመነጭ ተቻችሎና ተደጋግፎ የመኖር የጋራ እሴቶችን ገንብተዋል። በዚህም በየዘመኑ ያጋጠሟቸውን ፈተናዎች በጽናት በመሻገር እስከዛሬ እንደ ሕዝብ በሰላም አብሮ መኖር ችለዋል። ወቅቶች የሚፈጥሯቸውን ተግዳሮቶች ተሻግረውም ዛሬ ላይ ደርሰዋል።

የሕዝቦቹን የጋራ ጥቅሞች መገዳደር የሚፈልጉ ኃይሎች ዘመን የተሻገረውን የአገራቱን ግንኙነት አደጋ ውስጥ በመክተት ከዚሁ እኩይ ሥራ ተጠቃሚ /አትራፊ/ ለመሆን ተኙተው ያደሩበት ቀርቶ ያሸለቡበት ጊዜ የለም ። ኮሽ ባለ ቁጥር ኮሽታዎችን ከማስተጋባት ጀምሮ ኮሽታዎችን ለመፍጠርም ሲጥሩ ተስተውሏል።

በየዘመኑም የተሳካላቸው እስኪመስላቸው ረጅም መንገድ ተጉዘዋል። ይሁንና የአገራቱና የሕዝቦቹ የትስስር ገመድ በቀላሉ የሚበጠስ ባለመሆን ሳይሳካላቸው ቀርቷል። በየወቅቱ የደገሷቸው የጥፋት ድግሶችም በአገራቱ ሕዝቦች አስተዋይነትና አርቆ አሳቢነት እንዲሁ ባክነው ቀርተዋል።

የእነዚህ ኃይሎች የማያቋርጥ የጥፋትና የሴራ መንገድ ዛሬም መልኩን ሳይቀይር በየአደባባዩ መታየትና መደመጥ ከጀመረ ውሎ አድሯል። ለሱዳን ወንድሞቻችን ከእኛ በላይ አሳቢ ሆነው ለመገኘት እየሄዱበት ያለው መንገድ ታሪክን በአደባባይ ከመካድ ባለፈ፤ ለሱዳን ሕዝብ ከበሬታ ያጡ ስለመሆናቸው አመላካች ነው።

ከቅኝ ገዥዎች አስተሳሰብና ከዚህ አስተሳሰብ በሚመነጩ ሴራዎች የሚታመኑት እነዚህ ኃይሎች፤ ዛሬም አፍሪካውያን እንደ አንድ ሕዝብ ከፍ ያለ ዋጋ ያስከፈለውን የዚህ ሙት አስተሳሰብ አቀንቃኝ በመሆን የሁለቱን አገራት ህዝቦች ዘመን የተሻገረ ጉርብትና ችግር ውስጥ በመክተት፤ ከግጭቶች ለማትረፍ ባላቸው አቅም እየሰሩ ነው።

በአንድ በኩል በሱዳን ያለውን የፖለቲካ ትኩሳት፤ በሌላ በኩል በኢትዮጵያ ያሉትን ወቅታዊ ሁኔታዎች እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም፤ የአገራቱን ሕዝቦች ወደ ግጭት በመግፋት፤ የግጭቱ አትራፊ ለመሆን እያደረጉት ያለው ጥረት ከሁሉም በላይ የቱን ያህል የቅኝ ገዥዎች አስተሳሰብ ሰለባ ስለመሆናቸው አመላካች ነው።

የሁለቱ አገራት ሕዝቦች ከግጭት ለማትረፍ የሚካሄዱ ንግዶች ፍጻሜያቸው የቱን ያህል አስከፊ እንደሆነ በአግባቡ ይረዳሉ፤ በእነዚህ የግጭት ነጋዴዎች አንቱታ ያተረፉ አገራት የድንጋይ ክምር ሆነው፤ ሕዝቦቻቸውም በቋንቋ ተነግሮ ለማያልቅ መከራና ስቃይ ተዳርገው አይተዋል።

ዛሬ ላይ የአገራቱን ሕዝቦች ወደ ግጭት ለመክተት የሚደረጉ ሴራዎች በየትኛውም መንገድ ሆነ መመዘኛ ለችግሮቻቸው ዘላቂ መፍትሄ ሊያስገኙ የሚችሉና የቀደመውን ዘመን ጉርብትናቸውን የሚመጥንም አይደለም። ከዚህ ይልቅ “ውሻ በቀደደው ጅብ ይገባል “እንደሚባለው ራሳቸውን ለከፉ በላተኛ አሳልፎ የመስጠት ያህል ነው።

የአገራቱ ሕዝቦች ግንኙነት በታሪክ አጋጣሚ መጥተው በሚሄዱ መንግስታትና እነሱ በሚፈጥሯቸው ያልተገቡ ችግሮች የሚፈተንና ለገዥዎችም የጊዜ መግዣ ሽቀጥ ሆኖ የሚያገለግልም አይደለም።

የኢትዮጵያ እና የሱዳን ሕዝቦች ችግሮቻቸውን በሰላማዊ መንገድ በውይይት መፍታት የሚያስችል የዳበረ አቅም፤ ለዚህ የሚሆን ማህበራዊ፣ መንፈሳዊ እና ባህላዊ እሴቶች ባለቤትም ናቸው። ከሁሉም በላይ ደግሞ ተነጋግሮ መግባባት የሚያስችል የጋራ እጣ ፈንታ የሚጋሩ ሕዝቦች ናቸው።

በተለይም ቀጣይ እጣ ፈንታቸው በዓባይ ውሀ ላይ የተመሰረተ መሆኑ፤ ይህንም ተጨባጭ እውነታ እውን ለማድረግ እንደ ሕዝብ ቁርጠኛ መሆናቸው፤ ወቅታዊ ችግሮችን በቀላሉ ተሻግሮ መሄድ የሚያስችል ከፍ ያለ አቅም ይፈጥርላቸዋል።

ሕዝቦቹ አሁን ያጋጠማቸው ችግር የግጭት ነጋዴዎች እንደሚያጯጩሁት ሳይሆን፤ ቁጭ ብለው በስክነትና በሰላም ተነጋግረው የሚፈቱት ነው። የሚደርሱበትም መፍትሄ ለሌሎች መማሪያ የሚሆንና የቀደመውን ጉርብትናቸውን ከፍ ወዳለ ደረጃ የሚያሻግር እንደሚሆንም ጥርጥር የለውም!።


ኢፕድ

**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

# ከ“በፍፁም አይደገምም!“ ወደ “ይደገም፤ ይደገም ...!!!“

ግርማ መንግሥቴ

ቸገር ያለ ጊዜ ሲያጋጥም ሀሳብም አብሮ ቸገር ማለቱ የግድ ነው። በመሆኑም፣ ቸገር ያለ ጉዳይ ሲያጋጥም ደግሞ የባሰውኑ ሁሉም ነገር ቸገርገር ይልና ነገር አለሙ ሁሉ ድብልቅልቅ ይላል። ያኔ ወደ ኋላ መለስ ብሎ ማሰብ የግድ ይሆንና ይመጣል። የነገሮችን፣ ክስተቶችን ... ታሪካዊ ዳራ መፈተሽ የማይታለፍ ሆኖ ከተፍ ይላል።

በርእሳችን ላይ ትኩረት የሰጠነው ”በፍፁም አይደገምም!” (Never Again) እዚህ እንደ ጠቀስነው ጉዳዩ ቀላል አይደለም። ይዘቱ እንደ ቅርፁ ሳይሆን ከዛም በላይ የተራመደ፤ የሰውን ልጅ ሁሉ በአንድነት አንድ (ቢያንስ በጊዜው) ያደረገ፤ በታሪክ መዝገብ ላይ በወርቅ ቀለም የተፃፈ፤ የነበረውን የአለም ታሪክ ባልነበረ መልኩ ይቀይረዋል ተብሎ የተጠበቀ የአለም መንግስታት ውሳኔ (እና የቃል ኪዳን ሰነድ) የነበረ ውል ነው። ለምን?

እንደሚታወቀው፣ ሁለተኛው የአለም ጦርነት የሰውን ልጅ ቅርጥፍ አድርጎ የበላ ጦርነት ነው። ታሪኩን በገራገር ቋንቋ እንደ ወረደ ስናስቀምጠውም፣ ”ከ1932 ዓ.ም. እስከ 1937 ዓ.ም. ድረስ የተደረገ ታላቁ አለም አቀፍ ጦርነት ነው፤ በዚህ ጦርነት መጨረሻ የአክሲስ ሃያላት ማለትም ጀርመን፣ ጣልያንና ጃፓን ተሸነፉ። በጠቅላላ አለም ዙሪያ 70 ሚልዮን ሕዝብ በጦርነቱ ጠፋ። ከ20 ሚልዮን ህዝብ በላይ ለከፋ የአካል ጉዳት ተዳረገ። ከጦርነቱም በኋላ አሜሪካና ሶቭየት ኅብረት የዓለም ዋና ኃያላን ሆኑ። በሁለተኛው የአለም ጦርነት ወቅት ዋናው ተዋናይ ሂትለር ነበር።” የሚል ሆኖ ነው የምናገኘው።

በዚህ ምክንያት የአለም መንግስታት አንድ ነገር (ስምምነት?) ላይ መድረስ እንዳለባቸው ተገነዘቡ። በመሆኑም አንድ ድምዳሜ ላይ መድረስ ያለባቸው መሆኑንም ተረዱ። ያ ከላይ የጠቀስነው በሁለተኛው የአለም ጦርነት ሳቢያ የደረሰው ሰብአዊና ቁሳዊ ውድመት መደገም የሌለበት መሆኑን አመኑ። በዚሁ ምክንያትም ”መቸም አይደገምም” (Never Again) ሲሉ ተማማሉ። ”መቸም አይደገምም!!!” አሉ፣ የእምነት ቃላቸው፣ የአንገት ማተባቸው እስኪመስል ድረስ።

እውቁ የፊዚክስ ሊቅ አልበርት አንስታየን ”በሶስተኛው የአለም ጦርነት አሸናፊው ማን ይሆናል ብለህ ትጠብቃለህ?” ተብሎ ሲጠየቅ ”እሱን ተውትና የአራተኛውን ልንገራችሁ” ይላል። ”እሺ እሱን ንገረን” ሲባል ”በዛን ጊዜ ማንም አይኖርም፤ አይተርፍ” ብሎ መለሰ። ይህም እነሆ በጦርነት ታሪክ መዝገብ ላይ ተጠቃሽ ጥቅስ ሆኖ ተመዝግቦለት ይገኛል። ይህ የአንስታየን ምሁራዊ ትንበያ፣ ገና ያኔውኑ ”መቸም፣ መቸም አይደገምም” (Never Again) የሚለው የመሪዎች ምህላ ”ፌዝ” መሆኑ እንደገባው ያሳያልና እውነትም አንስታየን ሊቅ ነበር።

ከዚሁ ከጦርነትና እርስ በርስ መተላለቅ ጉዳይ ሳንወጣ አንድ ሌላ ተጠቃሽ ጥቅስን እናንሳ። እሱም የእውቁ የቀድሞው የኩባ ፕሬዚዳንት ፊደል ካስትሮ ንግግር ነው።

ካስትሮ ”የሚያስፈልገው የሀሳብ ጦርነት (Battles of Ideas) እንጂ የቴክኖሎጂ ጦርንት አይደለም። እንደ አለመታደል ሆኖ ግን አለም ምርጫው ያደረገው ሁለተኛውን ነው። ይህ ደግሞ ውጤቱ የከፋ እንጂ በፍፁም ለሰው ልጅ የሚመቸው አይሆንም” ነበር ያሉት። ይህ ጉዳዩ በተነሳ ቁጥር ሳይጠቀስ የማይታለፈው የካስትሮ ጥቅስ ዛሬ ላይ ሆኖ ለተመለከተው ያንኑ፣ ከላይ የጠቀስነውን ”መቸም፣ መቸም አይደገምም” (Never Again) በሚገባ የተረዳና የማይተማመን ኋደኛ በየወንዙ ይማማላል እንዲሉ፣ ገና ከመነሻው እማይረባ ብቻ ሳይሆን እማይሰራ መሆኑን አስቀድመው የተረዱ ስለመሆናቸው ጥሩ ማሳያ ነው። (እዚህ ላይ ጉዳዩን አፍሪካዊ እናድርገውና የአፍሪካ ህብረት በ2023 የመደበኛ ስብሰባውን መሪ ቃል ”በ2020 በአፍሪካ የነፍጥ ድምፆችን ጭጭ ማድረግ” የሚል የነበረ ሲሆን፤ መሪዎቹም ጉባኤውን ያጠናቀቁት በየአገራቸው ይህንኑ ተግባራዊ ለማድረግ በመስማማት መሆኑን አስታውሰን እንለፍ።)

በግልፅ መነጋገር ያስፈልጋልና ዛሬ ”መቸም፣ መቸም አይደገምም” (Never Again) የሚለው የማይረቡ ኋደኛሞች ምህላ፤ በ”ይደገም፣ ይደገም ...!!!” ተተክቷል የሚሉ አጥኚዎች ቁጥራቸው እየበዛ ብቻ ሳይሆን ወደ መድረክም በብዛት እየመጡና ተከታዮችንም እያበዙ እንደሚገኙ ማረጋገጫው ብዙ ነው።

አስተያየት ሰጪዎቹ ”Again and A gain” ያሉት፤ እኛ በሙዚቃ ኮንሰርት ሙድ ”ይደገም፣ ይደገም ...!!!” ያልነው እንደው ዝም ብለን ”ዘፈን ለማሞቅ” ወይም ጨዋታ ለማሳመር አይደለም፤ መሬት ላይ ያለው እውነታ፣ እየሆነና እየተደረገ ያለው ድርጊት ... ይህንኑ ስለሚያረጋግጥ ብቻ ነው።

ልብ እንበል፤ ከሁለተኛው የአለም ጦርነት ከተጠናቀቀና ”መቸም አይደገምም” (Never Again) ምህላ ከተፈፀመ በኋላ ምን ምን ተግባራት ተፈፀሙ? ብለን ብቻ እንጠይቅ። መልሱንም ምን ያልተፈፀመ ነገር አለን? ለዛውም ”ይደገም ይደገም ...!!!” በሚመስል መልኩ ሆኖ ነው የምናገኘው።

ሊቢያ አፈር ነህና .... እንደ ተባለው ሁሉ አፈር ሆናለች፣ ሶሪያ ከ”አለች” ይልቅ! ”የለችም” በሚባለው ደረጃ ላይ ነች፣ ናጄሪያ ቦኮ ሀራም ሲፈልግ የሚያርሳት፣ ሲፈልግ የሚቆፍራት አገር ነች፤ ደቡብ ሱዳን ... ዝም ነው። ሩዋንዳ . . . ምን ሆኖ ነበር? (ባህላዊው ድምፃዊ ”... ምን ልበላችሁ (2 ጊዜ)/ ታውቁት የለም ወይ በ’የቤታችሁ” እንዳለው ነው)፤ አፍጋኒስታን ... ቆጥረን አንጨርሰውም። ወዳለንበት ወቅታዊ ሁኔታ እንመለስ።

ያለንበት ሁኔታ ከአለማችን ሰላማዊው ቀጣና ይልቅ ሰላም ያልሆነው እየበዛ ያለበት ነው። ያለንበት ሁኔታ ከተስፋ ይልቅ ተስፋን የሚያጨልም የሚመስል ነው። ያለንበት ሁኔታ ፍርደ ገምድሉ በዝቶ ፍርድ የናፈቀበት፤ ፍትህና ርትእ ከነበሩበት የተሰደዱ እስኪመስል ድረስ ለሽታ እንኳን የታጡበት ነው።

ያለንበት ሁኔታ የሰው ልጅ ወጥቶ ለመግባት አይደለም ሳይወጣም እንኳን መኖር ያልቻለበት ነው። ያለንበት ሁኔታ ”ወንድም በወንድሙ ላይ ...” እንዲሉ ወንድም በወንድሙ ላይ የተነሳበት ነው። ያለንበት ሁኔታ ”መቸም፣ መቸም አይደገምም” (Never Again) ወደ ”ይደገም፣ ይደገም ...!!!” የተቀየረበት፤ ተቀይሮም ስራ ላይ ”በስፋት” እያዋለ ያለበትና ”ተጠናክሮ የቀጠለበት” ነው። ያለንበት ሁኔታ ... (ኢትዮጵያ ሳትቀር ”መቸም መቸም አይደገምም” (Never Again) በማለት የቀይ ሽብር ሰማእታት ሀውልትን ብትገነባም)፤ ... ያለንበት ሁኔታ ...

ከላይ ”ፍርደ ገምድል”ነትን በተመለከተ አንስተናልና እሱን አስመልክተን አንድ ሀሳብ ብቻ ጣል አድርገን ጽሑፋችንን እንቋጭ።

በብዙዎቻችን እንደታመነውና ጉዳዩ የሚመለከታቸውም በመረጃና ማስረጃ አስደግፈው እንደ ሚነግሩን፤ ”ፍርደ ገምድል”ነት የዘመኑ ፋሽን ሲሆን፤ የዳቦ ስሙም ”Both-side-ism” ይባላል።

እንደ ተመራማሪዎቹ ብያኔ ”Bothsidism” ማለት ሁለት ተፋላሚ ወገኖችን እኩል አድርጎ የማየት፣ ጥፋተኛውን ለይቶ ”አንተ ጥፋተኛ ነህ” ማለት አለመቻል፤ ሲያስፈልግ ሁለቱንም እኩል ጥፋተኞች አድርጎ የማየት፣ ሲያስፈልግ ደግሞ ሁለቱንም ’ትክክል ናችሁ’ ብሎ የመበየን ... አዲስ የፖለቲካ ፈሊጥ ነው፤ አላማውም በእጅ አዙር የራስን ጥቅም ማስከበርና ለዚህም ሁለቱን ተፋላሚ ወገኖች ጭዳ (የጦስ ዶሮ) የማድረግ የዘመኑ ”ብልጦች” አካሄድ ነው።

እዚህ ላይ ግን አንድ ነገር ማንሳትና ለውይይት አቅርቦ መሄድ ያስፈልጋል። እነዚህ ሁለት ተፋላሚዎች፣ ለ”Bothsidism” ኢሰብአዊ ፍልስፍና አራማጆች ጥቅም ሲባል ጭዳ እየሆኑና የሚሆኑ ወገኖች መቼ ነው የሚነቁትና ሕዝባቸውን ከሰላምና ፀጥታ ስጋት ነፃ የሚያደርጉት የሚለው ነው ! መልካም ጊዜ።

# ከስህተቶቻችን መማር ለምን አቃተን?

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ዛሬ ስለ ለውጥ ህግ እናወራለን:: የለውጥ ህግ የህይወት ህግ ነው:: የህይወት ህግ ደግሞ የአጠቃላዩ እንቅስቃሴአችን ህግ ነው:: ህይወት ሶስት ቀን ናት.. ትላንት ዛሬና ነገ :: ትላንት ዛሬን የምናደምቅበት ብዕራችን ነው :: ነገ ደግሞ ምን እንደሆነ የማናውቀው ለእያንዳንዳችን ባዳ ቀን ነው :: እኚህ ሶስት የጊዜ ፈረቃ በህይወታችን ላይ ያላቸውን ተጽዕኖ እየገለጥን እንይ:: ከዚም በመነሳትም አለም ሁለት አይነት ሰዎች አሏት ለማለት እንደፍራለን ፤ከትላንት የሚማሩና ትላንትን የሚያማርሩ:: ከትላንት የሚማሩ ሁሌም አሸናፊዎች ናቸው::

የዚህን አለም ብርቱና ስኬታማ ሰዎች ብታስተውሉ በትላንት ተምረው ዛሬን መልካም ያደረጉ ናቸው:: በእኛ ሀገር እየሆነ ያለው ግን ከዚህ በተቃራኒ ነው..ትላንትን ለመማረሪያ እንጂ ለመማሪያ ስናደርገው አንታይም:: የዛሬ ችግሮቻችንን ከትላንት አብራክ ውስጥ ጎርጉረን ያወጣናቸው ናቸው:: በትላንት የዛልን፣ በትላንት የምንኖር ህዝቦች ነን:: ሰው ትላንትን መርሳት ካልቻለ ዛሬ አይኖረውም:: ሰው መኖር የሚጀምረው ትላንትን መርሳት ሲችል ብቻ ነው::

ትላንት ከትዝታ ባለፈ በእኛ ህይወት ላይ ህላዊ የለውም:: አብዛኞቻችን በትላንት ዛሬን የምንኖር ነን:: ለዛም ነው እንደ ሀገር ከስረን የቆምነው:: ትላንት ለዛሬ የሚሆን ጉልበት የለውም:: እንድንማርበትና ዛሬን መልካም እንድናደርግበት መጥቶ የሄደ እንጂ በቁጭትና በሮሮ እንድናስታውሰው ሆኖ የተፈጠረ አይደለም:: እኛ ኢትዮጵያውያን ከትላንት ብንማር የሚያስተምሩን በርካታ ታሪኮች ነበሩን:: ግን አንማርም..ዛሬን በትላንት መንፈስ የምንኖር ነን::

በትላንት ጉያ ውስጥ የተደበቁ ብዙ የአንድነት ታሪኮች፣ ብዙ የመለያየት ታሪኮች አሉን:: የሚጠቅመንን እየወሰድን የማይጠቅመንን መተው አናውቅበትም:: ዛሬዎቻችን በትላንት ቁርሾ፣ በትላንት የፖለቲካ ርዮተ አለም የተጨማለቁ ናቸው:: አዲስ ዛሬ መፍጠር አልቻልንም:: ሰው ከትላንት ተምሮ አዲስ ዛሬን መፍጠር ካልቻለ ህልውናውን አደጋ ላይ እየጣለ ነው የሚሄደው:: ስህተት የሰውን ልጅ ካላወጠው በምንም አይለወጥም:: ትላንት መጠቶ የሄደው እንድንማርበት ነው:: በትላንት ችግሮቻችን መማር ካልቻለን የምድርን ትልቁን የለውጥ ህግ ዘንግተናል ማለት ነው::

ለምን ስልጣኔ ራቀን ? ፊት ተፈጥረን ለምን ኋላ ቀረን? ለዛሬ የሚሆን አዲስ ልብ ስለሌለን ነው:: ችግሮቻችንን ችግር ፈጣሪ በሆነ ሀሳቦቻችን ለመፍታት ስለምንሞክር ነው:: በመሰረቱ ችግር.. ችግር ፈጣሪ በሆነ ጭንቅላት አይፈታም:: የመፍትሄ ስፍራው ምክንያታዊ አእምሮ ነው:: ጭንቅላታችን በትላንትና በአምና የፖለቲካ አስተሳሰብ ተመርዞ፣ በትላንት የታሪክ ቁርሾ ተይዞ ከፍ ማለትም ሆነ ለችግሮቻችን መፍትሄ መውሰድ አንችልም:: ለአስተዋይ ሰው በስህተት ውስጥ መፈጠር ልክ በሆነ ነገር ላይ ከመፈጠር የበለጠ አዋጭ ነው::

ብዙዎቻችን ስህተት የሚያበላሸን እንጂ የሚሞርደን አይመስለንም:: ለዚህም ነው በእውቀት ድርቀት የምንሰቃየው:: ስህተት ዋጋ ቢስ የሚሆነው የማንማርበትና የማንለወጥበት ከሆነ ብቻ ነው:: እውቀት የትም አለ፣ የሰው ልጅ የትም፣ በማንም ሊማር ይችላል:: በስህተት ውስጥ የመማርን ያክል እውቀት ግን የትም አይገኝም:: እንከን አልባ እውቀት አንድ ጊዜ ነው የሚቀርጸን የስህተት እውቀት ግን እድሜአችንን ሙሉ የሚከተለን ፍጹምናችን ነው::

እኛ ግን ከስህተቶቻችን አንማርም:: ትላንትን ዋና የችግሮቻችን ምንጭ አድርገን የምንገልጥ ነን:: ስህተት ካልተማርንበት ሌሎች ችግሮችን እየፈጠረ የመከራ ሎሌ ነው የሚያደርገን:: የሰው ልጅ ደግሞ ትላንትን እያስታወሰ እንዲቆዝም ሳይሆን በዛሬ በረከት ተደስቶ ተመስገን እያለ እንዲኖር ነው ሰው የሆነው::

በህይወታችን የትኛውም ቦታ ላይ በስህተት ውስጥ ካላለፍን ምሉ አንሆንም:: ሳንገዳገድ መቆም አንችልም:: በአንድ ነገር ላይ የበላይ ስንሆንና ሀይልን ስንላበስ የትም ቦታ ላይ ያለአንዳች ተግዳሮት እንፈሳለን:: ይሄ ደግሞ በስህተት ውስጥ የመፈጠር ልዕልና ነው:: አንዳንዶች በችግራቸው ሌላ ችግር ይፈጥራሉ፣ አንዳንዶች ደግሞ በችግራቸው ነጋቸውን ብሩህ ያደርገሉ:: በችግራቸው ችግር የሚፈጥሩ ሰዎች የእውቀት ባይተዋር ናቸው::

በችግራቸው የሰላምን ግንብ ገንብተው የሚኖሩ እነሱ ደግሞ መለኛ ናቸው:: እኛም ለድህዋ ሀገራችን መለኛ መሆን ይጠበቅብናል:: በችግራችን ላይ ሌላ ችግር ሳይሆን ችግሮቻችንን የምንሽርበት የመነጋገርና፣ የመወያየት ብልሀትን የእኛ ማድረግ ይጠበቅብናል:: መንግስት እንደ መንግስት፣ ህዝብም እንደ ህዝብ ከችግሩ ተምሮ ለሰላም የሚሆን አቅም፣ ለአንድነት የሚሆን ሀይል ማጎልበት አለበት::

ጥበቦቻችን በትላንት አስተሳሰብ ታውረው የዛሬን በረከት ማየት ካልቻሉ እንደ ለመድነው ከጦርነትና ከመጠላላት አንወጣም:: ጦርነትና እኔነት ባህላዊ ጨዋታችን እስኪመስሉ ድረስ ለዘመናት ኖረንባቸዋል:: ኢትዮጵያዊነት መገዳደል እስኪመስል ድረስ ለዛውም ከወንድሞቻችን ጋር፣ ለዛውም እኛ ከምንላቸው ጋር ደም ተቃብተናል:: ሰው በሰላም ዋርካ ስር መጠለል ሲገባው በመከራ ሮሮ ውስጥ መውደቁ ተገደናል :: ችግሮቻችን ብልህ እንዲያደርጉን እንጂ ሞኝ እንዲያደርጉን መፍቀድ የለብንም::

አለም የስህተት መልክ ናት:: ስህተት ነው እንዲህ ጠፍጥፎ ያበጃት:: የአሁኑ ውብ መልኳ በስህተት ውስጥ የተፈጠረ ነው:: አለም የብዙ ትውልዶች አስተሳሰብ፣ የብዙ ሀሳቦች የስህተት ነጸብራቅ ናት:: በተለያየ ዘመን የመጡ አስተሳሰቦች፣ በተለያየ ዘመን የመጡ አመክንዮ ሀሳቦች አንዱ በአንዱ ላይ የበላይ በመሆን የፈጠሯት ናት:: እያጠፉ የሳሏት፣ እያደመቁ ያደበዘዟት የልክነትና የስህተት ቅይጥ:: አለም እኮ ዛሬም ድረስ ተሰርታ አላለቀችም.. ዛሬም ድረስ ተስላ አልተጠናቀቀችም:: እኛም በብዙ ስህተት ውስጥ አልፈን ነው ዛሬን ያየነው::

ስህተት ውስጥ ጥበብ አለ:: ውድቀት ውስጥ መስፈንጠር አለ:: እኛም ከትላንት እየተማርን፣ ካለፈው እየተረዳን ዛሬን በዋጋ መኖር ግድ ይለናል:: ጠቢብ ሰው ማለት መከራ የማይደርስበት ማለት ሳይሆን ከመከራው ተምሮ አዲስ ዛሬን የሚፈጥር ማለት ነው:: እኛስ ምን አይነቶች ነን? እንደሚታወቀው የሀገራችን አብዛኞቹ ችግሮች ከትላንት ማህጸን ውስጥ የሚመዘዙ ናቸው:: ይህ ማለት ዛሬም ድረስ ከትላንት አስተሳሰብ አሎጣንም ማለት ነው:: ይህ ማለት ዛሬም ድረስ እንደትላንቱ ነን ማለት ነው:: እንደ ሀገር ከትላንት እኩይ አስተሳሰብ መለየት ይኖርብናል:: እንደ ህዝብ፣ እንደመንግስት ትላንትን በይቅርታ የሚሻገር አእምሮና ልብ ልናዳብር ይገባል ::

ሰው በእውቀት ሲዘመን፣ በስልጣኔ ሲቀድም ነገ ላይ በኩራት የሚያወራውን ታሪክ ዛሬ ይሰራል እንጂ በትላንት ጦስ ዛሬን አይኖርም:: ዛሬ ለሁላችንም አዲስ ቀን ነው:: ስለምንድነው በትላንት ነውር ዛሬአችንን የምናጨልመው? ስለምንድነው በአንድ አይነት አስተሳሰብ አንድ አይነት ሆነን የምንኖረው? ይሄ ሁላችንም ጠይቀን የምንመልሰው የጋራ ጥያቄአችን ነው:: ከትላንት አስተሳሰብ ለመውጣት የዛሬን ዋጋ መረዳት ይኖርብናል:: ከትላንት አስተሳሰብ ለመመለስ መንግስትና ህዝብ አዲስ ነገር መናፈቅ ይኖርባቸዋል::

ከትላንት የጦርነት አስተሳሰብ ለመላቀቅ የትላንትን ቁስል የሚያሽር የፖለቲካ ስርዐት መገንባት ይኖርብናል:: ትላንትን መማሪያ እንጂ መማረሪያ ያላደረገ ትውልድ ሀገራችን ያስፈልጋታል:: እኛ ኢትዮጵያውያን ፖለቲካ ያመረቀዘው የብሄር ቁስል አለብን:: እኔነትና ተረኝነት የወለደው የመገፋፋት ህመም አለብን:: ራስ ወዳድነትና ጎጠኝነት የጸነሰው የመጠላላት ነቀርሳ አለብን:: ከነዚህ ደዌአችን ለመፈወስ ደግሞ ትላንትን ገሎ መቅበር አለብን:: ከነዚህ ደዌአችን ለመዳን እንደ ትላንት ያልሆነ አእምሮና መንፈስ ያስፈልገናል::

ሰው ወደ ትላንት ሲሳብ የዛሬን በረከት አይደርስበትም:: ስልጣኔ ሊርበን ይገባል:: እድገትና ዘመናዊነት ሊጠማን ይገባል:: ይሄን ሁሉ ዘመን ኋላ ቀርተን እንኳን በሌሎች መቀደማችን አይቆጨንው:: በማይጠቅመን ነገር ያባከነው ጊዜ ሊቆጨን ይገባል:: አንድነት አጥተን የተገፋፋንባቸው ጊዜአቶች ሊያስቆጩን ይገባል:: ትውልድ ካልተቆጨ፣ መንግስት ካልተቆጨ፣ ህዝብ ካልተቆጨ ከትላንት አስተሳሰብ መላቀቅ አይችሉም:: የሀገራችን ሰላም ማጣት፣ የህዝባችን ኋላ መቅረት፣ የፖለቲከኞቻችን አለመግባባት ሊቆጨን ይገባል::

የትውልዱ ብሄር ተኮር አስተሳሰብ፣ በትላንት አስተሳሰብ ዛሬን መኖራችን ሊቆጨን ይገባል:: የስኬት ህግ አስተሳሰብን መሰረት ያደረገ ነው:: የለውጥ ህግ አምናን ሳይሆን ዘንድሮን፣ ትላንትን ሳይሆን ዛሬን የተንተራሰ ነው:: እኛንም ሆነ ሌሎችን የምንቀይረው በአስተሳሰባችን ስንቀየር ነው:: ህይወታችንንም ሆነ ሀገራችንን የምንቀይረው ከማይጠቅሙን አፍራሽ አመለካከቶች ስንርቅ ነው:: ዛሬ ላይ የሀገራችን መልክ ወያባ ነው:: የእርቅና የይቅርታ ሀሳብ አጥታ ሀገራችን ጠውልጋለች:: የውይይትና የተግባቦት መድረክ አጥቶ ህዝባችን ተጎሳቁሏል:: ዳገቱን እናልፍ ዘንድ አዲስ አስተሳሰብ ያስፈልገናል:: ከነበርንበት ዝቅታ ከፍ እንል ዘንድ እውቀት መር የህይወት ልምድ ግድ ይለናል::

ህይወታችንን ከትላንት በመማር እናለምልም:: ሀገራችንን ከትላንት በመማር እናሻግር:: የዚህ አለም ከባዱ ጥፋት ትላንትን ዛሬ ላይ መድገም ነው:: ሰው የትላንቱን ጉስቁልና ዛሬ ላይ ከደገመው፣ የትላንቱን ስህተት ዛሬ ላይ ከመለሰው እንደ ትላንቱ ሆኖ ከመኖር ባለፈ አዲስነት አይጎበኘውም:: ነውር እየመሰላቸው መሳሳትን አጥብቀው የሚፈሩ ብዙ ሰዎች አሉ:: ስህተትን በመፍራት ተጠንቅቀው የሚረግጡ፣ ተጠንቅቀው የሚኖሩ፣ አድብተው የሚንቀሳቀሱ ብዙ ናቸው:: እኚህ ሰዎች ሳያውቁ ራሳቸውን ከጥበብ ያራቁ ናቸው ::

ስህተትን በመፍራት መናገር ያቆሙ፣ መጠየቅ እርም ያሉ፣ መሞከርና መጀመር የፈሩ ብዙ አሉ:: ስህተት አያስፈራም የሚያስፈራው ከስህተት አለመማርና አንድ አይነት ሆኖ መኖር ነው:: የሚያስፈራው በአንድ ጥፋት ሁልጊዜ እየተጸጸቱ መኖር፣ ሁልጊዜ እያለቀሱ መኖር ነው:: የሚያስፈራው በአዲስ አስተሳሰብ ከዘመኑ ጋር አብሮ አለመራመድ ነው:: የሚያስፈራው የዛሬን አዲስ ማለዳ በትላንት ጨለማ መሰወር ነው:: የሚያስፈራው ሀገርና በአዲስ ልብ፣ ህዝብን በአዲስ ተስፋ አለማሻገር ነው::

ህይወት ትምህርት ቤት ናት:: ጊዜ ደግሞ መምህራችን:: እኛ ደግሞ ተማሪዎች:: በዚህ የተፈጥሮ ሂደት ውስጥ ነን:: በህይወት ትምህርት ቤት ውስጥ ጊዜ ሲያስተምረን ጥሩ ተማሪ መሆን ግዴታችን ነው:: ጊዜ ሲያስተምረን ጥሩ ተማሪ አለመሆን ማለት ለመውደቅና ለመሸነፍ መዘጋጀት ማለት ነው:: አለም ደግሞ ለተሸናፊዎች ቦታ የላትም:: አለም የባለራዕዮች ናት::

> **ህይወት ትምህርት ቤት ናት:: ጊዜ ደግሞ መምህራችን:: እኛ ደግሞ ተማሪዎች:: በዚህ የተፈጥሮ ሂደት ውስጥ ነን:: በህይወት ትምህርት ቤት ውስጥ ጊዜ ሲያስተምረን ጥሩ ተማሪ መሆን ግዴታችን ነው:: ጊዜ ሲያስተምረን ጥሩ ተማሪ አለመሆን ማለት ለመውደቅና ለመሸነፍ መዘጋጀት ማለት ነው አለም ደግሞ ለተሸናፊዎች ቦታ የላትም:: አለም የባለራዕዮች ናት**

አለም ራሳቸውን ለመቀየር ከሌሎች ጋር ለሚተባበሩ የተገለጠች ናት:: አለም ተነጋግረው ለሚግባቡ ነፍሶች የተሰጠች ናት:: አለም በትጋትና በጥረት ከፍ ለማለት ለተሰናዱ የተዘጋጀች ናት:: የእኛ ጥሩ ተማሪ መሆን ጥሩ ሀገርና ጥሩ ትውልድ በመፍጠር ሂደት ላይ የአንበሳ ድርሻ አለው:: ጥሩ የህይወት ተማሪ መሆን ማለት ከትላንት ተላቆ ዛሬን ብቻ መኖር ነው:: ጥሩ ተማሪ መሆን ማለት ከዘልማድ ወጥቶ እውቀት መር በሆነ እሳቤ ሀገርን ማራመድ ነው:: ጥሩ ተማሪ መሆን ማለት ጥላቻን በይቅርታ መሻር ማለት ነው::

በየትኛውም የህይወት ስፍራ ውስጥ ትልቅ ነገር ለማግኘት ስንነሳ የምናጣው ትንሽ ነገር ይኖራል:: አላማችን ትልቁን ነገር ማግኘት እስከሆነ ድረስ የምናጣው ትንሽ ነገር ሊያስቆጨን አይገባም:: አላማችን ሊሆን የሚገባው በትልቅ ሀሳብ ትልቅ ነገር ማግኘት ነው:: በይቅርታ ማሸነፍ ነው:: ዘመኑ በከሸፈ ሀሳብ የምንራመድበት ሳይሆን በታደሰ ሰውነት አንድነትን የምናጠናክርበት ነው::

አሁን ላይ እየባከንን ነው:: በትላንት ዛሬን መኖር አልቻልንም:: እጃችን ላይ ያለውን ውድ ነገር በርካሽ እየቀየርን ነው:: ወርቃችንን በጠጠር እየመነዘርን ነው:: ቁራ ማግኘት ርዕግባችንን እየሸጥን ነው:: ምን እንደሚያስፈልገን ማወቅ አልቻልንም:: የትላንት ስህተቶቻችንን ዛሬም በመድገም ላይ ነን:: ለሰላም ስንደክም፣ ለአንድነት ስንበረታ አንታይም:: ችግሮቻችን ሌላ ችግር ሲፈጥሩብን እንጂ ሰላም ሲያወርዱልን አናይም:: ከስህተቶቻችን መማር ለምን አቃተን?!።

# "ሃምሳ ሎሚ ........."!

እፀገነት አክሊሉ

"ሃምሳ ሎሚ ለአንድ ሰው ሸክሙ ለሃምሳ ሰው ጌጡ " ይላሉ አበው ሲተርቱ፤ አዎ ምንም ነገር ቢሆን ከተረዳዱበት ሸክሙ ይቀላልለ፤ ውጤቱ ያማረ ይሆናል:: አንድ ሰው ምን ጠንካራ ቢሆን፣ ገንዘብ፣ ሃብት፣ ንብረት፣ ጉልበትና እውቀት ያለው ቢሆን፤ አንድ ሰው አንድ ነው፤ ብቻውን ምንም ማድረግ አይችልም፤ ላድርግ እንኳን ቢል ውጤቱ ላይ መንገራገጮች አያጡትም:: ነገር ግን ያ አንድ ሰው የተሸከመውን ሸክም ሲካፈሉት ነገሩ ይቀላል፤ ስራው ይቃናል፤ ውጤቱም ያማረ ይሆናል::

ወይዘሮ በቀለች ተሾመ እድሜያቸውን ሙሉ የኖሩት አዲስ አበባ ከተማ ልዩ ስሙ አዋሬ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ነው:: እዛው አግብተው ሰባት ልጆችን ወልደዋል:: ዛሬ ላይ ሶስቱ በህይወት ባይኖሩም የተቀሩት አራቱ ልጆቻቸውን እንዲሁም የልጅ ልጆቻቸውን ይዘው ይኖራሉ:: ወይዘሮ በቀለች ከባለቤታቸው ጋር አቅማቸው የፈቀደውን የቀን ስራ እየሰሩ ልጆቻቸውን ያሳድጉ ቤታቸውን ያስተዳድሩ ነበር:: ኋላም ባለቤታቸው በሞት ሲለዩዋቸው ጉሊት በመነገድ የቤተሰቡን ጉሮሮ መሙላት የኑሯቸው መንገዱ ነበር::

ዛሬ አቅማቸው ደክሟል ለዘመናት የኖሩባት ቤትም እንደእሳቸው አርጅታ በላያቸው ላይ ልትወድቅ ተቃርባ ነበር፤ በምኑም በምኑም እየተጠገነች ግን ዛሬ ላይ ደርሳለች:: ወይዘሮ በቀለች ከልጆቻቸው እንዲሁም ከልጅ ልጆቻቸው ጋር በጋራ የሚኖሩባት ደሳሳዋ ጎጇቸው ዛሬ ላይ ቀን ሊወጣላት ብርሃን ልታይ እሷም እንደ ሌሎች ቤቶች ቤት ተብላ ልትጠራ ተራዋ ደረሰና እነሆ በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ አይን ውስጥ ገባች::

"....እኔ የዘንድሮውን ክረምት ከነልጆቼ እንዴት እወጣዋላሁ ብዬ ሰግቼ ነበር ግን ጥሎ የማይጥለው አምላክ ተመለከተኝና ዶክተር ዐቢይ አሕመድ መጥተው ቤታችንን ቀና ሊያደርጉልን፤ ከብርድ ከዝናብ ከውሃ ሊታደጉን ፈቀዱ፤ ይህ ለእኔ እንደገና መወለድ ነው " ይላሉ::

አዎ ምንም ለሌላቸው ለወይዘሮ በቀለች ከእንደገና መወለድም በላይ ነው:: የሚያፈስ ጣሪያ የፈረሰ ግድግዳ የጨቀየ መሬት ቀና ብሎ ሊሰራ መሆኑን ማሰብ በራሱ ትልቅ ነገር ነው::

እንደ ወይዘሮ በቀለች ሁሉ ወይዘሮ ባዝወርቅ ፍትሃተ በዚሁ በአዋሬ ላይ እድሜያቸውን ሙሉ የኖሩ እናት ናቸው:: ወይዘሮ ባዝወርቅ እንደ ዛሬው ጉልበታቸው ሳይደክም ማየትም ሳይሳናቸው በፊት ከመርካቶ የታሰረ ቆጮ እያመጡ አዋሬ ገበያ ላይ በመነገድ ታዋቂም ነበሩ:: ዛሬ ግን ያ ሁሉ ነገር የለም በልጆቻቸውና የልጅ ልጆቻቸው እጅ ላይ ወድቀዋል፤ ማየትም ስለማይችሉ እንደ ልባቸው ወጥቶ መግባት ተስኗቸዋል::


ወይዘሮዋ ለዓመታት የኖሩባት ቤት እንደሳቸው አርጅታ አቅም ቢሳናት ማፍሰስም፤ ብርድ ማስገባትም ጀምራ ነበር:: ነገር ግን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከሚያድሷቸው ቤቶች ውስጥ የእሳቸውም አንዱ ሆኗል:: በዚህም በጣም ደስተኛ ናቸው::

" .....ቤቴ በላዬ ላይ ሳይወድቅ በፊትም መንግስት ደርሶልኛል:: በዚህም ፈጣሪዬን አመሰግናለሁ:: አሁን የምፈልገፈው ነገር የለም" ይላሉ::

ድር ቢያብር አንበሳ ያስር ነውና ብሂሉ መንግስት በዚህም መልኩ የችግረኛ እናቶችን ቤት ሲያድስ ልበ ቀና ኢትዮጵያውያን ደግሞ ቤቱ ታድሶ እስኪጠናቀቅ ድረስ ሰዎቹ ማረፊያ እንዳይቸገሩ በማለት በራሳቸው ተነሳሽነት ወጪ እያወጡ ቤት እየተከራዩ እያስቀመጧቸው ነው::

አዎ! ኢትዮጵያዊነት ምስጢሩ ጥልቅ ነው የሚባለው ለዚህ ነው:: ኢትዮጵያዊ ወገኑ ተቸግሮ ብቻውን አይበላም፤ እንዲህ ባለው ሁኔታ ደግሞ እንኳን አዛውንቶች ሌላውንም ቢሆን ለመርዳት ከችግሩ እንዲያገግም ድጋፍ ለማድረግ ምንም የሚሳነው ነገር የለም::

ወይዘሮ በቀለች እንደሚሉት ዶክተር ዐቢይ መጥተው ቤቶቹን ሊያድሱልን ስራውን ሲያስጀምሩ በጣም ደስተኛ ሆነን ነው የጠበቋቸው:: ለማረፊያ ይሆነን ዘንድም እዛው አካባቢ ቤት እንድንከራይ ነግረውናል፤ ነገር ግን እኔ ቤት ተከራይቼ መቆየት አቅም አልነበረኝም:: እናም እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያሉ ደግ ልብ ያላቸው ወጣቶች በተለይም አቶ ዮሃንስ እና ጓደኞቹ መጥተው እኛስ ምን እናግዛችሁ ሲሉ በጣም ነው የተደሰትኩት ይላሉ::



ወይዘሮ በቀለች ተሾመ

ፎቶ፡- ገበበ ገብሬ



ወይዘሮ ባዝወርቅ ፍትሃተ



አቶ ዮሃንስ እርገጤ

ወይዘሮ በቀለች ደጋግ ኢትዮጵያውያንን ያቆይልን ቤታችን ለእድሳት ቢፈርስም ማረፊያ አላጣንም አራት ሺ ብር እየከፈሉልን እየኖርን ነው፤ ከዚህ በላይ ደግነት ከወዴት ይመጣል ይላሉ:: ምናልባት እነዚህ ወጣቶች ልበ ቀና ሆነው ይህንን ባያደርጉልን ኖሮ ቤታችን ታድሶ እስከሚያልቅ እንቸገር ነበር፤ አሁን ግን ስራውም ቶሎ ቶሎ እየተሰራ ነው እኛም እስከ አሁን የሚሞቅ ቤት ውስጥ ቁጭ ብለናል በማለት ከብዙ ምርቃት ጋር ሃሳባቸውን ይገልጻሉ::

ወይዘሮ ባዝወርቅም በበኩላቸው አይናቸው የማያይ ደካማ ከመሆናቸው ጋር ቤታቸው በጠቅላይ ሚኒስትሩ መታደሱ ደስ ቢያሰኛቸውም ስራው እስኪጠናቀቅ ድረስ የት አርፋለሁ? የሚለው ነገር አሳስቧቸው እንደነበር ይናገራሉ::

ሆኖም አቶ ዮሃንስና ጓደኞቹ እኛም የበኩላችንን በማድረግ የራሳችንን ችግር በራሳችን እንፈታለን ብለው መጥተው ሲያናግሯቸው ድርብ ደስታ እንደተሰማቸውም ይናገራሉ:: ዛሬ ምንም ስጋት የለብኝም የሚሉት ወይዘሮ ባዝወርቅ ቤቴ ታድሶ እስከሚጠናቀቅ ከነልጆቼ በሞቀ ቤት ውስጥ እንድቆይ ተደርጌያለሁ፤ ለእኔ ከዚህ በላይ እንደገና መወለድ የለም፤ ለሰጪዎቻችን ሁሉ ፈጣሪ ብድሩን እጥፍ አድርጎ ይስጣቸው፤ አገራችንን ሰላም ያድርግልን በማለት ሃሳባቸውን ይገልጻሉ::

አቶ ዮሃንስ እርገጤ በአዋሬ አካባቢ የሚኖርና የእነ ወይዘሮ በቀለች ጎረቤት ነው:: አቶ ዮሃንስ አንድ ቀን ጠዋት ወደስራ ሲወጣ ዶክተር ዐቢይ አካባቢው ላይ ደርሰው የአቅመ ደካሞችን ቤት እድሳት እያስጀመሩ መመልከቱን ይገልጻል:: ሰዎቹንና ቤታቸውን እንዲሁም ኑሯቸውን በቅርብ የሚያውቀው አቶ ዮሃንስ አዛውንቶቹ የዚህ እድል ተጠቃሚ መሆናቸው እጅጉን እንዳስደሰተው ይናገራል::

አቶ ዮሃንስ እንደሚለው አንድ ጠቅላይ ሚኒስትር ወርዶ እንደዚህ አይነት ልብ የሚነካና አርዓያነት ያለው ተግባር ሲፈጽም ከእኔ ከተራው ዜጋስ ምን ይጠበቃል ? ማለቱንም ያስታውሳል::

ቤቱ ለእድሳት በፈረሰበት ወቅትም ወደአዛውንቶቹ በመሄድ እንኳን ደስ አላችሁ ማለቱን የሚናገረው አቶ ዮሃንስ ሆኖም አዛውንቶቹ በተደረገላቸው ነገር ላቅ ያለ ደስታ ቢሰማቸውም ቤቱ ተገንብቶ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ግን የሚያርፉበት ቦታ አሳስቧቸው እንደነበር ያስታውሳል::

"......በወቅቱ ሄጄ እንኳን ደስ ያላችሁ! ስላቸው በከፍተኛ ደስታና ምርቃት ውስጥ ሆነው መደሰታቸውን ገለጹልኝ፤ ሆኖም ግን አዛውንቶች ገቢያቸውም ቤት ተከራይቶ ለአንድ ወር እንኳን ለመቆየት የሚያስችል ባለመሆኑ ስጋት ውስጥ እንዳሉም ገለጹልኝ፤ ይህ እኔስ በአቅሜ ምን ላደርግና ይህንን ስራ ልደግፍ እችላለሁ የሚል ሃሳብ ወደአእምሮዬ እንዲመጣ አደረገኝ" ይላል::

በቀጥታ ከአዛውንቶቹ ቤት ወጥቼ ያደረኩት የምቀርባቸው ጓደኞቼ ጋር መደወል ነበር የሚለው አቶ ዮሃንስ በዚህም ለደወልኩላቸው ሁሉ ያለውን ነገር አስረድቻቸው ስጋቱንም ነገርኳቸው፡፡ እነሱም መንግስት ይህንን ያህል ርቀት ሄዶ ስራዎችን በተለይም አቅመ ደካሞች የሚታገዙበትን ነገር ሲያደርግ እኛ የሁለትና የሶስት ወር የቤት ኪራይ መክፈል አያቅተንም ቤት ፈልገህ አስገባቸው በማለት ወዲያውኑ አዋጥተው 19 ሺ ብር ላኩልኝ በማለት ይናገራል::

በወቅቱ አቶ ዮሃንስ ወይዘሮ ባዝወርቅን ብቻ ነበር ለመርዳት ይህንን ገንዘብ ያሰባሰበው ነገር ግን ወይዘሮዋ እንደኔ አቅም የሌላት አብራኝ የኖረች እኔ ያለእሷ እሷም ያለእኔ መኖር የማንችል ጎረቤቴ አለች እሷን ጨምረህ አግዘን በማለታቸው ወይዘሮ በቀለችም የእድሉ ተጠቃሚ መሆን ቻሉ::

አቶ ዮሃንስ እንደሚለው ሰው ከተረዳዳ እንኳን ይህች ትንሽ ነገርና ብዙ ተዓምራትን መስራት ይችላል፤ እኔም ያደረኩት ይህንን ነው :: ጠቅላይ ሚኒስትሩ እየሰሩ ያለው የበጎ ተግባር ስራ ሁላችንንም ሊያነቃቃ ይገባል፡፡ እሳቸው አንድ ሲያደርጉ እኛ ደግሞ ከስር ስንደግፍ ብዙ ችግሮቻችን ውሃ ይበላቸዋል ሲል ይናገራል::

‹‹እኔና ጓደኞቼ ከቤተሰብ ርቀን ያለን ነን፡፡ እኛ እዚህ አቅመ ደካሞችን ባለችን ነገር ስንደግፍ የእኛ ቤተሰቦች ባሉበት የሚደግፉ ሌሎች ሰዎች ፈጣሪ ያዘጋጃል:: በሌላ በኩል እኔ እዚህ ጋር መልካም ስራ ስሰራ የሚያየኝ ልጄ ነገ እሱም ሲያድግ አገሩ ላይ ችግር ፈጣሪ ሳይሆን የመፍትሔ አካል ይሆንልኛል፡፡ እናም ሁሉም ሰው በየአቅራቢያው ያለውን አንድም ሁለትም ሰው ቢያግዝ ከእኛ የሚተርፍ ችግር አይኖርም ››በማለት ይናገራል::

ከአቶ ዮሃንስ ጋር በበጎ ስራው ከተሳተፉት አምስት ጓደኞቻቸው መካከል ኢንጂነር መስፍን ውብሸት አንዱ ናቸው:: ኢንጂነር መስፍን ስለ ስራቸው ስጠይቃቸው አይ እኔ ሳልሆን ባለቤቴ ናት መናገር ያለባት አሉኝ፡፡ ባለቤታቸው ወይዘሮ ብሩክታዊት ጌታሁን እንዳሉት በጎነት ለራስ ነው:: አንድ ሰው ሰው ነው ለመባል የሚበቃውን አጠገቡ ያለውን ችግር በሚችለው አቅሙ ማቃለል ሲችል ነው ይላሉ::

በጎነት በገንዘብ ብቻ የሚገለጽ አይደለም የሚሉት ወይዘሮ ብሩክታዊት ሰው ጊዜውን ጉልበቱን እንዲሁም ቀና ሃሳቡንም በመስጠት በጎነቱን ማረጋገጥ ይችላል:: እኛም ካለችንና ከተሰጠችን ላይ መንግስት ይህንን የአቅመ ደካሞችን ቤት በዚህ መልኩ ሲሰራ እኛ ደግሞ ቤቱ እስኪያልቅ ማረፊያ ብንከራይላቸው ችግሩን ተካፈልን ማለት ነው በሚል በአቶ ዮሃንስ አነሳሽነት እንደተሳተፉም ይናገራሉ::

"ምናለኝና ምን እሰጣለሁ" ይላል አንዳንድ ሰው ያሉት ወይዘሮ ብሩክታዊት መስጠት ከሀብት ጋር የሚገናኝ አይደለም፡፡ መልካምነትና ንጹህ ህሊና ያለው ሁሉ ያልተሰጠው ነገር የለም፤ በመሆኑም እሱን ማካፈል ላይ ነው ስራ መሰራት ያለበት:: በሌላ በኩልም ለምሳው የያዛት አንድ ዳቦ ግማሿን ቢያካፍል ያ ሰው ያለውን አካፍሏል፡፡ ስለዚህ ደግነትን ከመኖር እና አለመኖር ጋር ማገናኘት አያስፈልግም ይላሉ::

ኢትዮጵያውያን ሲፈጥረን መልካም ነን፡፡ በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ችግርን እስከታች ወርዶ የሚያይ መንግስት ሲኖር ደግሞ ተደጋግፎ ሁኔታዎችን ለማለፍ መጣር ነገ ጥቅሙ ዘርፈ ብዙ ነውና ሁሉም ያለውን ቢያካፍል ችግሮችና መከራዎቻችን ታሪክ ይሆናሉ ሲሉ መልዕክታቸውን ያስተላልፋሉ::

# ወጣቶች

## ትልቅ ዓላማ ይዘው ትንሽ ድጋፍ ያጡ ወጣቶች

**አስናቀ ፀጋዬ**



የወጣትነት እድሜ ብዙ ስራ የሚሰራበት ነው:: ትኩስ ጉልበት ያለውም ከወጣቱ ዘንድ በመሆኑ በዓለም ዙሪያ በየግዜው ጠንካራና አስደማሚ ስራዎች ይሰራሉ:: በርካታ ሀገራትም በወጣቶች ላይ ትኩረት አድርገው በመስራታቸው የብልፅግና ማማ ላይ ወጥተዋል:: የዛሬዎቹ የዓለም ሀያል ሀገራት አሜሪካና ቻይናም የወጣት ተኮር ስራ ውጤት ናቸው::

ወጣቶች ሀገርን ሊለውጥ የሚችል ጉልበት ፣ እውቀት፣ ሃሳብና የስራ ፈጠራ ክህሎት አላቸው:: ነገሮችን በፍጥነትና በጥራት የማከናወን ብቃትም ተክነዋል:: በተለይ ደግሞ ለቴክኖሎጂ ቅርብ በመሆናቸው ዓለምን የሚቀይሩ በርካታ የስራ ፈጣራ ውጤቶችን ጀባ ብለዋል::

በኢትዮጵያም በርካታ ቁጥር ያለው ወጣት ቢኖርም እንደ አንድ አንጡራ ሃብት በሚገባ ጥቅም ላይ እየዋለ አይደለም:: እንደሀገር ለወጣቶች የሚሰጠው ትኩረትም እዚህ ግባ የሚባል አይደለም:: በወጣቱ ላይ ትኩረት ተደርጎ ቢሰራ ግን ሀገሪቱን በልዩ ልዩ መንገድ መቀየር እንደሚቻል እሙን ነው:: ለዚህም መንግስት የአንበሳውን ድርሻ ይወስዳል::

የመንግስት ድርሻ እንዳለ ሆኖ ታዲያ አንዳንድ ወጣቶች በራሳቸው ተነሳሽነት በተለያዩ የስራ ዘርፎች ላይ ተሰማርተው ከራሳቸው አልፈው ወገናቸውንና ሀገራቸውን ሲጠቅሙ ይታያል:: በተለይ ደግሞ በእነርሱ እድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ወጣቶች የእውቀት አድማሳቸው ሰፍቶ ቀጣይ ሕይወታቸው የተቃናና ለሀገራቸውም በጎ አሳቢ እንዲሆኑ የሚታትሩ አልጠፉም:: ለዚህም ድጋፍ አጥተው አቋረጡት እንጂ እነ ወጣት ኑሪያ የጀመሩት ሃሳብ ትልቅ ማሳያ ነው::

ተማሪ ኑሪያ አሚር የዚህ ሃሳብ ጠንሰሽና መስራች ከሆኑት ተማሪዎች ውስጥ አንዷ ናት:: በአዲስ አበባ ረጲ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት የአስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪ ስትሆን የንባብ ባህልን ያዳበረችው ገና በልጅነቷ ነው:: ይህ የማንበብ ልምድ ታዲያ በሂደት ዳብሮ የኮሮና ወረርሽኝ በኢትዮጵያ በተከሰተበት ወቅት ከሌሎች ሁለት ጓደኞቿ ጋር በመሆን ቤተ መፅሃፍት ለመክፍት አግዟታል::

በዚህም በወረርሽኙ ምክንያት እቤት ተቀምጠው የነበሩ በርካታ ተማሪዎች ቤተ መፅሃፍቱን ለመጠቀም እድል ከፍቶላቸዋል:: መፅሃፍ የማንበብ ልምዳቸውን ለማዳበርም በእጅጉ ረድቷቸዋል:: በተለይ ደግሞ በጀሞ ሁለት አካባቢ አንድ ብቻ ቤተ መፅሃፍት የነበረ በመሆኑ ይታይ የነበረውን የቤተ መፅሃፍ እጥረትም መቅረፍ ችሏል:: በዋናነት ደግሞ በጋራ መኖሪያ ቤቶች አካባቢ የሚኖሩ ተማሪዎች ቤተ መፅሃፍትን በአቅራቢያቸው አግኝተው እንዲጠቀሙ አስችሏቸዋል::

እርሷና ጓደኞቿ ጀሞ አካባቢ የጋራ መኖሪያ ቤት ላይ ተከራይተው የከፈቱት ቤተ መፅሃፍት ለተከታታይ ስድስት ወራት ዘልቆ የነበረ ቢሆንም በገንዘብ እጥረት ምክንያት ከዚህ በላይ ሊቀጥል አልቻለም:: ወትሮም ቢሆን ቤተሰብ እያስቸገሩ የቤተ መፅሃፍቱን ኪራይ ሲሸፍኑ የቆዩ ቢሆንም በመጨረሻ አቅማቸው ተሟጦ ቤተመፅሃፍቱን ለመዝጋት ተገደዋል::

ተማሪ ኑራና ሁለቱ ጓደኞቿ ቤተ መፅሃፍታቸው ተዘግቶ አገልግሎት ቢያቆምም ያለስራ ከመቀመጥ በጥቂቱም ቢሆን አንባቢውን ማህበረሰብ ይጠቅማል በሚል በተለያዩ አጋጣሚዎች በራሳቸው ጥረትና በስፖንሰር ድርጅቶች አሰባሰበዋቸው የነበሩትን አንድ ሺ መፅሃፍቶች ለአብርሆት ቤተ መፅሃፍት በቅርቡ አበርክተዋል::

ምንም እንኳን በገንዘብ እጥረት ምክንያት የቤተመጽሀፍቱ አገልግሎት ቢቋረጥም ኑራና ጓደኞቿ የጀመሩትን ትልቅ አላማ ከግብ ለማድረስ ይፈልጋሉ:: ለዚህም በተደጋጋሚ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን የመንግስት አካላትንና የግል ተቋማትን በር ቢያንኳኩም እስካሁን ድረስ በቂ ምላሽ አላገኙም:: አላማቸው ቤተመፅሃፍትን ማቋቋም ብቻ ሳይሆን በወጣቶች ዙሪያም ትላልቅ ስራዎችን የመስራት ፍላጎት ያላቸው በመሆኑ ጉዳዩ የሚመለከተቻው አካላት ለወጣቶቹ በቂ ምላሽ እንደሚሰጧቸው ይጠበቃል::

ተማሪ መሰረት አሰፋም የዚህ ቤተመፅሃፍት መስራች ስትሆን ልክ እንደ ኑራ ሁሉ በረጲ ሁለተኛ ደረጃና የመሰናዶ ትምህርት ቤት የአስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪ ናት:: ቤተመፅሃፍቱን የማቋቋሙን ሃሳብ እርሷና ጓደኞቿ የጀመሩት ገና የአስረኛ ክፍል ተማሪ እያሉ ነው:: ግዜው የኮሮና ወረርሽኝ የተከሰተበት በመሆኑ ተማሪዎች ትምህርት ቤት የሚሄዱት በሳምንት ሶስት ቀን በመሆኑና የቀረውን ግዜ በእረፍት ስለሚያሳልፉ በዚህ ግዜ ተማሪዎች በትርፍ ግዚያቸው መፅሃፍት በማንበብ እንዲያሳልፉ ቤተ መፃህፍት የመክፈት ሃሳብ መጣላቸው::

የቤተ መፅሃፍቱ መከፈት በአካባቢው ያሉ ተማሪዎችን ከመጥቀም በዘለለ ተማሪ መሰረትና ጓደኞቿ በወቅቱ አስረኛ ክፍል የነበሩ በመሆናቸው ለብሄራዊ ፈተና ጥሩ ዝግጅት እንዲያደርጉ ረድቷቸዋል:: በቤተሰቦቻቸው ዘንድም ሃሳቡ ትልቅ ተቀባይነት በማግኘቱ አስፈላጊው ድጋፍና ማበረታቻ ተደርጎላቸዋል::

ገና ቤተ መፅሃፍቱን የመክፍት ሀሳቡን እንደጠነሰሱ በቅድሚያ የሄዱት የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ባህልና ቱሪዝም ፅህፈት ቤት ሲሆን ሃሳባቸውም ወዲያውኑ ተቀባይነት አግኝቷል:: ቤተ መፅሃፍት ለማቋቋም የሚያስችል ህጋዊ ሰውነት ከፅህፈት ቤቱ ካገኙ በኋላ የተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ጋር በመሄድ መፅሃፍቶችን ማሰባሰብ ችለዋል:: በተለይም ከኢትዮጵያ አየር መንገድና ከወመዘክር መፅሃፍቶችን በማሰባሰብ ቤተመፅሃፍቱን አቋቁመው ወደ ስራ ገብተዋል::

በጋራ መኖሪያ ቤቶች ላይ በርካታ ተማሪዎች ይኖራሉና፤ ቤተመፅሃፍቱንም ይጠቀማሉ በሚል የጀመሩት የቤተመፅሃፍት አገልግሎት መጀመሪያ ተማሪዎች ቤተመፅሃፍቱን እስኪለምዱትና የማንበቡንም ልምድ እስከሚያዳብሩ በነፃ ይገለገሉ ነበር:: በሂደት ግን ሃሳባቸው ተማሪዎቹ እየከፈሉ ቤተመፅሃፍቱን እንዲገለገሉ የነበረ ቢሆንም ይህ ባለመሳካቱ ቤተመፅሃፍቱ በቤተሰባቸው ድጋፍ ኪራዩን እየሸፈነ ለስድስት ወራት ከቆየ በኋላ የገንዘብ እጥረት አጋጥሞት ስራውን አቁሟል::

‹‹በአሁኑ ግዜ ለአብርሆት ቤተ መፀሃፍት ከ አንድ ሺ በላይ መፃህፍትን አስረክበናል›› የምትለው ተማሪ መሰረት ይህንንም ያደረግነው የእኛ ቤተ መፀሀፍት ስራ በማቆሙ መፅሃፍቶቹ ያለስራ ከሚቀመጡ አብርሆት ገብተው አገልግሎት እንዲሰጡ መሆኑን ትገልፃለች::

በቀጣይም የሚመለከታቸው አካላት በማናገርና በመሰባሰብ ቤተመፃህፍቱን ዳግም ከማቋቋም በዘለለ ሁሉን አቀፍ የወጣቶች ማእከል ለማቋቋምና በተለያየ መልኩ ወጣቶችን የመታደግ ሃሳብ እንዳላቸውም ታስረዳለች:: በዚህ አጋጣሚ ወቅቱ ክረምት ነውና ወጣቶች አልባሌ ቦታ ከሚያሳልፉ ግዚያቸውን በንባብ እንዲያሳልፉ ትመክራለች::

ተማሪ ታሪኳ አብሼም እንዲሁ በረጲ ሁለተኛ ደረጃና የመሰናዶ ትምህርት ቤት የአስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪ ስትሆን ኑራና መሰረት ቤተመፀሃፍት ሲቋቁሙ እርሷም የበኩሏን ጥረት አድርጋለች:: እርሷና ጓደኞቿ የመሰረቱት ቤተ መፅሃፍት በሁለት እግሩ ከቆመ በኋላ በገንዘብ እጥረት መቆሙ ይቆጫታል:: ግን ደግሞ ከሚመለከታቸው አካላት በቂ ድጋፍ ቢገኝ ከዚህም የተሻለ ቤተ መፅሃፍትና የወጣቶች ማእከል መገንባት እንደሚቻል ታስባለች::

የተለያዩ ሀሳብና እቅድ ያለቻው በርካታ ወጣቶች አሉ የምትለው ተማሪ ታሪኳ፤ ወጣቶቹ ያሰቡት አላማና እቅድ እንዲሳካ ከበርካታ አካላት ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው ትናገራለች:: በተለይ ደግሞ መንግስት እንዲህ አይነት ወጣቶችን ሀሳብ መደገፍ እንዳለበት ትጠቁማለች::

‹‹የእኛም ሀሳብ ከዚህ የተለየ አይደለምና የሚመለከታቸው አካላት አላማችንን ሊደግፉን›› ይገባሉ ትላለች:: በተለይ ደግሞ እንዲህ አይነቱ ሀሳብ በወጣቶች ሁለንተናዊ ስብእና ግንባታ ትልቅ አስተዋፅኦ ያለው ከመሆኑ አንፃር ድጋፉ የግድ እንደሚያስፈልግ ትጠቁማለች:: እኛም እንዲህ አይነቱን ድጋፍ ብናገኝ ኖሮ የተሻለ ደረጃ መድረስ እንችል ነበር ስትል ትገልፃለች::

የእርሷና የጓደኞቿ ህልምም ቤተመፅሃፍቱን መልሶ ማቋቋም ብቻ ሳይሆን የወጣቶች ማእከልም ጭምር መገንባት በመሆኑ በርካታ ወጣቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ስለሚያስችል በዚህ አጋጣሚ መንግስት የተለያዩ ድጋፎችን ማድረግ እንደሚገባው ታመለክታለች::

ወጣቶችም ቢሆኑ አልባሌ ቦታ ከመዋል ይልቅ የክረምቱን ወቅት በንባብ ቢያሳልፉ ያተርፋሉ እንጂ አይከስሩም ትላለች:: ንባብ አንድም እውቀት ለመቅሰም ሁለትም የእረፍት ግዜን እየተዝናኑ ለማሳለፍ ስለሚጠቅም ወጣቶች የማንበብ ባህላቸውን ከወዲሁ ማዳበር እንዳለባቸውም ትጠቁማለች:: በዚህም የተሻለ ማንነታቸውን መገንባትና የህይወት አቅጣጫ ማየት እንደሚችሉ ትጠቅሳለች::

የወጣቶች ስብእና የሚገነባው በቤተሰብ፣ በትምህርት ቤትና በአካባቢ ማህበረሰብ ነው:: ከዚ ባሻገር ወጣቶች ስብእናቸውን የሚገነቡትና የእውቀት አድማሳቸውን የሚያሰፉት በንባብ ነውና ኑራ፣ መሰረትና ታሪኳ የጀመሩት ስራ እንደቀላል የሚታይ አይደለም:: እናም እንዲህ አይነት ተግባራት ለሀገርም ለወገንም ይጠቅማሉና መንግስት፤መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትና ባለሃብቶች አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍ ሊያደርጉ ይገባል የእለቱ መልእክታችን ነው:: ሰላም!!

**ንባብ አንድም እውቀት ለመቅሰም ሁለትም የእረፍት ግዜን እየተዝናኑ ለማሳለፍ ስለሚጠቅም ወጣቶች የማንበብ ባህላቸውን ከወዲሁ ማዳበር እንዳለባቸውም ትጠቁማለች**

# የምድር በረከት

# የጌጣ ጌጥ ማዕድናት በገበያ መመራት፤ እድልና ስጋት



**መሳኩ ኤርሴ**

ከማዕድናት መካከል የሰው ልጆች ለጌጣ ጌጥ ማዕድናት ልዩ ዋጋና ትርጉም ይሰጣሉ። ጌጣ ጌጥ ማዕድናት ቀለማቸው ቀልብን የሚስቡ፣ ውስጣዊ ደስታን የሚፈጥሩ በመሆናቸው ተፈላጊነታቸውና ተወዳጅነታቸው ከፍ ያለ ነው። ሰዎች ይጌጡባቸዋል ይዋቡባቸዋል። ከፍተኛ ዋጋም ያወጡባቸዋል። አገሪቷም የተለያዩ ጌጣጌጦችን ማምረት የሚያስችላት የከበሩ ድንጋዮች ባለቤት ናት። በኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ አካባቢዎች በርካታ የጌጣ ጌጥ ማዕድናት እንደሚገኙ መረጃዎች ያሳያሉ።

በኢትዮጵያ የጌጣጌጥ ማዕድናት በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች እንደሚገኙ መረጃዎች ቢያሳዩም አገሪቱ ከጌጣጌጥ ማዕድናቱ መጠቀም ያለባትን ያህል ተጠቃሚ መሆን ሳትችል ቆይታለች። የማዕድን ሚኒስትር ኢንጂነር ታከለ ዑማ በቅርቡ የ2014 በጀት ዓመት የ10 ወራት ዕቅድ አፈጻጸም ባቀረቡበት ወቅት እንደተናገሩት፤ 2317 ኪሎ ግራም ብቻ የጌጣ ጌጥ ማእድናት ናቸው ለውጭ ገበያ የቀረቡት።

አገሪቱ አላት ተብሎ ከሚታሰበው ከፍተኛ የጌጣ ጌጥ ማዕድናት ሀብት አንጻር ለውጭ ገበያ የቀረበው የጌጣ ጌጥ ማዕድናት መጠን እጅግ አነስተኛ ነው። አገሪቱ ከጌጣ ጌጥ ማዕድናት ተጠቃሚ መሆን ባለባት ልክ ተጠቃሚ እንዳትሆን ካደረጉት ምክንያቶች መካከል በምርት እና በግብይት ስርዓት ላይ የሚታዩ ችግሮች ናቸው።

አገሪቱ ከጌጣ ጌጥ ማዕድናት ተጠቃሚ መሆን ባለባት ልክ ተጠቃሚ እንዳትሆን እንቅፋት ከሆኑት ችግሮች መካከል በተለይም በማዕድናቱ የመንግሥት የዋጋና የደረጃ ተመን እንዲሁም ሌሎች አላስፈላጊ መስፈርቶች ተጠቃሽ ናቸው። የጌጣ ጌጥ ማዕድናት ግብይት ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመቅረፍ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መንግሥት የተለያዩ ጥረቶችን እያደረገ ይገኛል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘም ሰሞኑን ሚኒስትሩ በማህበራዊ ሚዲያ ገፃቸው ባጋሩት መረጃ፤ የጌጣ ጌጥ ማእድናት የግብይት ሰንሰለትን ለማቃለልና ኢትዮጵያ ከዘርፉ ማግኘት ያለባትን እንድታገኝ ከዚህ በፊት ሥራ ላይ የነበረውን በመንግሥት የዋጋና የደረጃ ተመን እንዲሁም ሌሎች አላስፈላጊ መስፈርቶች ተነስተው የንግድ ሥርዓቱ በገበያ ብቻ የተመራ እንዲሆን ወስነናል ሲሉ አስፍረዋል።

እነዚህ የጌጣ ጌጥ ማእድናት ከዚህ ቀደም የነበረው የመንግሥት ዋጋና የደረጃ ተመን እንዲሁም አላስፈላጊ መስፈርቶች ተነስተው የንግድ ስርዓቱ በገበያ ስርዓት ብቻ የተመራ እንዲሆን መወሰኑ አገሪቱ ከማዕድናቱ ማግኘት ያለባትን ጥቅም ማግኘት እንድትችል ከፍተኛ ፋይዳ እንደሚኖረው የምጣኔ ሀብት ምሁራን ያብራራሉ።

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አቶ ዳዊት ተሻለ እንደሚሉት የማዕድናት ግብይት በገበያ ስርዓት ብቻ እንዲመራ መወሰኑ ዘርፈ ብዙ ፋይዳ አለው። የማዕድናት የንግድ ስርዓት በገበያ ብቻ መመራት በጌጣ ጌጥ ማዕድናት ገበያ ተሳታፊዎች መካከል ነፃ ውድድርን ያበረታታል። የገበያ ውድድር ሲኖር በውድድሩ አሸናፊ ሆኖ ለመውጣት የገበያ ተሳታፊዎቹ ቅልጥፍና እና ፈጠራ የታከለበት አሰራር ለመከተል ይገደዳሉ።

የማዕድን ጌጣ ጌጥ ግብይት ላይ መንግሥት ዋጋ እና የደረጃ ተመን በሚያደርግበት ወቅት በዘርፉ የተሰማሩ አካላት ስኬታማነት የሚወሰነው በዘርፉ ተዋናዮች ጥረት ብቻ ሳይሆን፤ በመንግሥት ዋጋ እና ደረጃም የሚወሰን ነው። በዘርፉ ተዋናዮች ብቻ ስለማይወሰን የዘርፉ ተዋናዮች ያላቸውን ሙሉ አቅም ተጠቅመው እንዳይንቀሳቀሱ እንደሚያደርጋቸው ያነሳሉ።

አሁን ግን የንግድ ስርዓቱ በገበያ ብቻ ሲመራ የዘርፉ ተዋናዮች ስኬታማነት የሚወሰነው በዋናነት በራሳቸው በዘርፉ ተዋናዮች ጥረት ነው። ቅልጥፍና በታከለበት መንገድ የሚሰሩት ትርፋማ የመሆን እድላቸው ከፍ ያለ ይሆናል። በገበያው ስኬታማ ለመሆን የተለያዩ ፈጠራ የታከለበትን አሰራሮችን እንዲከተሉ ያነሳሳቸዋል። ፈጠራ ያልታከለበት አሰራር ተከትለው ውጤታማ ሊሆኑ አይችሉምና።

በዚህም በማዕድን ዘርፍ የተሰማሩ አካላት ብሎም አገሪቱ ተጠቃሚ ይሆናሉ። አገሪቱ ከዚህ ቀደም መሰል አሰራሮች ባለመዘርጋቱ ተጠቃሚ ሳትሆን የቆየችበትን ዘመን ለማካካስ የሚያስችል ሥራ ለመስራት ያስችላል።

አቶ ዳዊት እንደሚሉት፤ የግብይት ስርዓቱ በገበያ ስርዓት ብቻ የሚመሩ የጌጣ ጌጥ ማዕድናትም በጥንቃቄ ሊለዩ ይገባል ይላሉ። ሁሉም የጌጣ ጌጥ ማዕድናት ግብይት በገበያ ስርዓት ብቻ እንዲመራ የሚለቀቅ ከሆነ በአገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ አሉታዊ ጫና ሊያሳድር ይችላል። በአሁኑ ወቅት የአገሪቱ ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት የሆኑ ማዕድናት ከመንግሥት ቁጥጥር ውጪ ሊሆን አይገባም።

ለአብነት ያህል ወርቅ ለአገሪቱ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የሚያስገኝ ማዕድን ነው። የወርቅ ግብይት ግን ከገበያ ስርዓት ውጪ ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም ወርቅ የአገሪቱ የውጭ ምንዛሬ ግኝት መሰረት ነውና። ወርቅ የመንግሥትን ካዝና ከማሳደግ አልፎ ብዙሃኑን የሚጠቅም ነው። እንደ ወርቅ ያሉ ምርቶች ግብይት ላይ የመንግሥት ቁጥጥር ተጠናክሮ መቀጠል አለበት።

ከወርቅ ውጭ ያሉ እና እስካሁን ድረስ በሚፈለገው ልክ ጥቅም ላይ ያልዋሉ የጌጣ ጌጥ ማዕድናትም በገበያ ስርዓት ብቻ እንዲመራ በሚደረግበት ወቅት ጥንቃቄዎች ሊደረግ ይገባል። የጌጣ ጌጦቹ ግብይት በአቅርቦት እና ፍላጎት ብቻ እንዲመራ መደረግ አለበት ምንም አይነት ቁጥጥር ሊኖር አይገባም ማለት እንዳልሆነ ሊታወቅ ይገባል ይላሉ።

እንደ አቶ ዳዊት ማብራሪያ፤ መንግሥት እንደ መንግሥት ገብቶ ከመነገድ እና አላስፈለጊ መሰናክሎችን ከመፍጠር መውጣት አለበት ማለት በዘርፉ ምንም አይነት ቁጥጥር አይኑር ማለት አይደለም። በገበያ ብቻ እንዲሆን መደረጉ እንደመልካም ነገር የሚወሰድ ሆኖ የመንግሥት ክትትል እና ቁጥጥርም አስፈላጊ ነው። ነጻ ተብሎ ከመልቀቅ ይልቅ ቁጥጥር የሚያደርግ አካል ሊኖር ይገባል። በገበያ ብቻ ይመራ ሲባል በአቅርቦትና ፍላጎት ላይ ብቻ ይወሰን ማለት ነው።

ይህ ደግሞ የተለያዩ ህገ ወጥ ሥራዎችን ለሚሰሩ አካላትም በር ሊከፍት ይችላል። ቁጥጥር ካልተካሄደ በዘርፉ የተሰማሩ ነጋዴዎች ጌጣ ጌጦችን የሸጡበትን የውጭ ምንዛሬ ለህገ ወጥ አላማዎች ሊጠቀሙበት እንደሚችሉ የጠቆሙት አቶ ዳዊት፤ ቁጥጥር ማድረግ ከተቻለ አገሪቱ ተጠቃሚ ልትሆን ትችላለች። ዝም ብሎ ልቅ የሚደረግ ከሆነ ግን አደገኛ ችግር ይዞ ሊመጣ ይችላል። በተለይም ከዚህ ዘርፍ ግብይት የሚገኘው ገንዘብ ምን ላይ ይውላል የሚለውን መከታተል አለበት።

ችግሮች ከተከሰቱ በኋላ ከመሯሯጥ ይልቅ ከአሁኑ ሊታሰብበት ይገባል፤ እነዚህን ነገሮችን መቆጣጠር የሚቻለው የሚቆጣጠር አካል ሲኖር ነው የሚሉት አቶ ዳዊት፤ ለዚህም ተቋም ሊኖር ይገባል ይላሉ። በተለይም አገሪቱ ካለችበት ሁኔታ አንጻር በአግባቡ ቁጥጥር ተደርጎበት ለተገቢው ዓላማ ካልዋለ ለሌላ ዓላማ የመዋል እድሉ ከፍ ያለ ነው።

የማዕድን ዘርፍን ለማሳደግ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መንግሥት እየወሰዳቸው ያሉ እርምጃዎች ዘርፉ ለአገሪቱ ኢኮኖሚ ማበርከት ያለበትን ማበርከት እንዲችል ከፍተኛ እድል የሚፈጥሩ ናቸው። መንግሥት በጌጣ ጌጥ ማዕድናት የግብይት ስርዓት በገበያ እንዲመራ መተው እንደተጠበቀ ሆኖ የማዕድናቱን የምርት እድገት ሊያሳድጉ የሚችሉ እርምጃዎችን አጠናክሮ መቀጠል አለበት። በአገሪቱ የከበሩ የጌጣ ጌጥ ማዕድናት ምርትና ግብይት ላይ እየታዩ ያሉ ችግሮች የማዕድናቱ ግብይት በገበያ ስርዓት እንዲመራ በመተው ብቻ የሚፈታ አይደለም። የግብይት ስርዓቱ ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመፍታት በዘርፉ የተሰማሩ ባለድርሻ አካላት በጋራ የመስራት ልምዳቸውን ሊያዳብሩ ይገባል።

በዘርፉ የተሰማሩ አካላትን የማበረታታት ሥራዎች ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው። የባህላዊ የጌጣ ጌጥ ማዕድናት አምራቾች ማህበራትን ማጠናከር ወሳኝ ነው። ማህበራቱ የሚያጋጥማቸው እንቅፋቶችን ለማቃለል መንግሥት ትኩረት ሰጥቶ መሥራት አለበት።

የዘርፉ ችግር የግብይት ስርዓቱ በገበያ ብቻ እንዲመራ በመተው የሚፈታ አይደለም። ለዘመናት የተከማቹ ችግሮች ያሉበት ዘርፍ እንደመሆኑ ተጨማሪ እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው። በተለይም በዘርፉ ለተሰማሩ የህብረተሰብ ክፍሎች አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረጉን መቀጠል አለበት። በዘርፉ ለተሰማሩት አነስተኛ የማምረቻ መሳሪያዎች ከውጭ አገራት የሚገቡበትን አሰራሮች ማመቻቸትን ጨምሮ ሌሎች ድጋፎችን ማድረግ አለበት። መሰል ድጋፎች በመንግሥት በኩል የማይቀርቡ ከሆነ ዘርፉን በሚፈለገው ደረጃ ለማድረስ አዳጋች ይሆናል።

የጌጣ ጌጥ ማዕድናቱ እሴት ሳይጨመርባቸው ወደ ውጭ አገራት የመላክ ሁኔታ እንዲቀጥል ማድረግ በአገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ የሚያሳድረውን አሉታዊ ተፅዕኖ ከግምት በማስገባት መንግሥት የንግድ ስርዓቱን ከማመቻቸት ባሻገር መንግሥትም አገሪቱ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን የውጭ ምንዛሬ እንድታገኝ ማዕድናቱ እሴት ተጨምሮባቸው የሚወጡበትን መንገድ ቢያመቻች መልካም ነው።

በጌጣ ጌጥ ማዕድናት ልማት ላይ የሚሰማሩ ፕሮጀክቶች መንግሥት መሸፈን ያልቻለውን በመሸፈን ለበርካታ ሥራ ፈላጊ ወጣቶች የሥራ እድል የመፍጠር አቅም ያላቸው በመሆናቸው ማዕድን በአገርና በመንግሥት አቅም ብቻ ፈልጎ ማግኘት ከባድ በመሆኑ ፕሮጀክቶችን በማፈላለግ ከአጋር አካላት ጋር መሥራት ያስፈልጋል።

ዓለም አቀፍ ድርጅቶች እውቀታቸውን፣ ገንዘባቸውን እና የሥራ ባህላቸውን ይዘው እንዲመጡ እና ኢትዮጵያ ካላት የሰው ኃይልና የተፈጥሮ ሀብት ጋር ለማስተሳሰር በትኩረት መስራት አለበት።

በተግባር በጌጣ ጌጥ ማእድናት ሥራ ላይ የማይገኙ ግን በህገ ወጥ ሥራዎች ላይ ተሰማርተው ዘርፉን እየጎዱ ያሉ አካላትን ለህግ የማቅረብ ሥራዎች ሊታሰብበት ይገባል። ህገ ወጥ ማዕድን አዘዋዋሪዎች ላይ የሚወሰዱ ህግ የማስከበር እርምጃዎች መጠናከር አለባቸው። እርምጃዎቹ በመሰል ህገ ወጥ ተግባራት ላይ የሚሳተፉትን ሊያስተምር የሚችል ሊሆን ይገባል።

አገሪቱ የጌጣ ጌጥ ማእድናትን ወደ ውጭ አገራት በመላክ ተጠቃሚ እንድትሆን ለማስቻል ባለሙያዎችን በስፋት ማብቃት የግድ ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአንዳንድ ዩኒቨርሲቲዎች የማዕድን ዘርፉን የሚመለከቱ የትምህርት ክፍሎች ተከፍተው ማስተማር መጀመራቸው እና የነበሩትን የማጠናከር ሥራ መጀመሩ እንደመልካም ጅምሮ የሚታይ ነው። መሰል ሥራዎች በሌሎች ዩኒቨርሲቲዎችም ተጠናክሮ መቀጠል አለበት።

ከቅርብጊዜወዲህእየተፈጠሩያሉምቹሁኔታዎችን በመጠቀም በዘርፉ የተሰማሩ አካላት ማዕድናትን በጥሬው (እሴት ሳይጨመርባቸው) ለገበያ ከማቅረብ ይልቅ እሴት ጨምረው ለማቅረብ በትኩረት መስራት አለባቸው። የጌጣ ጌጥ ማዕድናትን ከመቁረጥ ውጭ ምንም ሳይጨምሩ ለገበያ የማቅረብ ሁኔታ እንዲቆም መደረግ አለበት። እሴት ተጨምሮባቸው ሲወጡ ለአገርም ሆነ ለማኅበረሰቡ የሚኖራቸው አስተዋጽዖ የጎላ ይሆናል።

የኢትዮጵያን የጌጣ ጌጥ ማእድናት እና ሌሎች የተፈጥሮ ሀብቶች ለዓለም ማስተዋወቅ ሥራ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ሊሰራ ይገባል። የጌጣ ጌጥ ማዕድናት ስኬት እውን የሚሆነው በመንግሥት እና በዘርፉ በተሰማሩ አካላት ጥረት ብቻ አይደለም። ማህበረሰቡም ከፍ ያለ ፋይዳ አለው። ማህበረሰቡም የሌሎች አገራትን የጌጣ ጌጥ ማዕድናት ከመጠቀም ይልቅ የአገራቸውን የጌጣ ጌጥ ማዕድናት በመጠቀም ለሌሎች አገራት ማስተዋወቅ ይጠበቅባቸዋል።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## ራስን ፍለጋ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵያ)**

ራሴ የጠፋብኝ ሰው ነኝ..ራሴን ካጣሁት ሰንበቻለው:: ማነህ ላለኝ ማቲያስ ነኝ እላለው እንጂ ማቲያስ ማን እንደሆነ አላውቀውም:: ሰው እንዴት ራሱ ይጠፋዋል? ስል እኔው በኔ እደነቃለው:: ሰው ራሱን አጥቶ ምንም ቢያገኝ እንደማይረካ አንድ ማለዳ ነው የተገለጠልኝ:: ‹እኔ ማነኝ? ለምንድነው ሰው የሆንኩት? ወደዚህ አለም ለምን መጣሁ? ብዬ ራሴን ጠይቄ መልስ ያጣሁ ጊዜ:: ከዚህ ጥያቄ በኋላ ነበር ራሴን ፈልጌ ማግኘት እንዳለብኝ የተሰማኝ::

አንድ ጊዜ አንድ ካፌ ቁጭ ብዬ መጽሀፍ አነባለው:: አጠገቤ ጸጉሩን ያንጨፈረረ ጆሮው ላይ ሎቲ የሰካ አንድ ደንደሳም ጎረምሳ ተቀምጧል:: የሰውነቱ ማማር ከሩቅ ይስባል:: ቅልብ ኮርማ ነበር የሚመስለው:: እንደ እኔ ያሉ አስር ኮሳሳዎችን የሰለቀጠ መሰለኝ:: ሰው አያይም.. አይኖቹን ስልኩ ላይ አፍጦ የሆነ ነገር ይጎረጉራል:: ፊቱ ላይ እየሄደ የሚመጣ ሳቅና ግርምት፣ ኩስተራና አርምሞ ተስሏል::

ከእሱ አጠገብ ደግሞ ከዘራቸውን ወንበር ላይ ያስደገፉ ባለ ነጭ ጸጉር አዛውንት ተቀምጠዋል:: ራሴን ፍለጋ ላይ ስለሆንኩ ሊያስተምረኝ ከሚችል ከማንኛውም ነገር ለመማር ዝግጁ ነበርኩ:: መጽሀፌን እየከደንኩ ሲያሰኘኝ እየከፈትኩ ዙሪያዬን መቃኘት ያዝኩ:: በዛ ሰፊ መናፈሻ ውስጥ እኔ፣ ደንደሳሙ ጎረምሳና አዛውንቱ በቅርብ ርቀት ላይ ተሰይመናል:: ወዲያው በአንዲት ፈገግተኛ አስተናጋጅ ተይዞ የሽማግሌው ምሳ መጣ:: ምሳው ጠረጴዛ ላይ ከማረፉ ከሽማግሌው አፍ አንድ ቃል ወጣ...‹እንብላ ልጆቼ› የሚል ቃል::

በዚያ ቅጽበት እያነበብኩ ነበርና ከማነበው መጽሀፍ ላይ ቀና ብዬ አየኋቸው:: እርጅና የተጫናቸውን፣ በነጫጭ የሽፋል ጸጉር የተከበቡ አይኖቻቸው ወርውረው አንዴ እኔን አንዴ ወጠምሻውን እያዩ አገኘኋቸው:: ምላሽ

> **ዛሬ ላይ በብዙ ነገራችን ተለያይተን የቆምነው የድሮ መልካም ባህሎቻችንን ስለተውን ነው:: በዘመን ውስጥ መብቀል እንዲህ አይደለም፣ ስልጣኔ የአባቶችን ስርዐት መተው አይደለም..ስልጣኔ ራስን ለዘመን ማዘጋጀት ሳይሆን ዘመንን ለራስ ማዘጋጀት ነው**

እየጠበቁ እንደሆነ ስለገባኝ...

‹አመሰግናለው አባቴ› ስል የድርሻዬን ተወጣሁ:: ራሱን ያጣ ሰው ነበርኩ..ለአንድ ሽማግሌ የሚሆን መልካም ቃል ከጠፋው ማንነቴ ውስጥ በማግኘቴ ደስታ ተሰማኝ:: ራሴን እያገኘሁት መሰለኝ..ላልገኝ እየጠፋሁም:: አይኖቼን የማነበው መጽሀፍ ላይ መልሼ የጠፋውን ራሴን ፍለጋ ስጀምር ከወጣቱ ጉሮሮ የወጣ የሚመስል ጎርናና ድምጽ ተሰማኝ:: ለሁለተኛ ጊዜ ቀና አልኩ:: ወጣቱ ወጠምሻ አይኖቹን ከሞባይሉ ላይ ሳይነቅል ‹ይሄ ነገር ዛሬም አልቀረም እንዴ ፋዘር? ሲል ሰማሁት::

‹ምኑ? ያልገባቸው ሽማግሌ መልሰው ጠየቁ::

‹እንብላ የሚለው ነገር ነዋ? አሁን እኮ 21ኛው ክፍለ ዘመን ላይ ነን›:: አለ:: አሁንም አላያቸውም.. አይኑ፣ ልቡ፣ ቀልቡ፣ መንፈሱ ሁሉ ሞባይሉ ላይ ነበር::

የትዝብት ሳቅ ሳቅ ብለው ‹የአሁኑ ትውልድ ጥሩ ነገር አታውቁም:: ለልጆቻችሁ ምን እንደምታወርሷቸው እግዜር ይወቀው:: እንብላ እኮ የኢትዮጵያዊነት ቀለም ነው:: ኢትዮጵያዊነትን ከነሙሉ ክብሩና ማዕረጉ የምታገኘው እዛ ውስጥ ነው:: ከትላንት ዛሬ የደረስነው አብረን እየበላን፣ አብረን እየጠጣን ነው:: ጣሊያንን ያሸነፍነው፣ በኡጋዴንና በአንባላጌ በካራማራም ድል ያገኘነው አብረን ስለበላን ነው:: የአባቶችህን ወግ ብታደምጥ ኖሮ ብዙ ቁም ነገር ትሰማ ነበር› ሲሉ በምሬት ተናገሩ::

ሽማግሌው ብቻ ሳይሆኑ እኔም ተገረምኩ:: እኔን እላለው እንጂ ለካ ከኔ በላይ ራሱን ያጣ ሰው አለ:: ለሀገሬ አዘንኩላት..ለካ ራሱን ያጣ መካን ትውልድ ነበር ታቅፋ የምትኖረው:: ሰው ራሱ ሲጠፋው እንደ እኔና ልክ እንደዚህ ወጣት ምንም ነው ስል አሰብኩ:: ከእሱ ግን እንደምሻል እርግጠኛ ነበርኩ:: እኔ ራሴ ብቻ ነው የጠፋኝ ይህ ወጣት ግን ታሪኩንም ነው ያጣው:: ከዛም አላረፍኩም ‹ዘመናዊነት ምንድነው? ስልጣኔስ? ስል ራሴን መጠየቅ ጀመርኩ:: ብዙ ጥያቄዎች በአእምሮዬ ውስጥ ተፈጠሩ:: መጽሀፌን ከድኜ ማሰላሰል ጀመርኩ::

አዛውንቱ አንዴም ወደ ምግቡ እጃቸውን አልዘረጉም:: እሳቸው የሚያውቁት ሀቅ አብሮ መብላት ነው:: እኔና ይሄ ወጣት ደግሞ በእሳቸው እውነት ላይ ቆመን የእሳቸውን እውነት የከዳን ወጥቶናል:: በየመሀሉ ቀና እያልኩ አያቸዋለው..ትውልድን የሚወቅስ ፊት ያስታቅፉኛል:: በመሀል ድምጻቸውን ሰማሁት..

‹ልጄ አትሳት..ዘመናዊነት አብሮነት ነው:: እኛ እጅ ካልሰጠን በቀር ባህል የሚሸር፣ ልማድ የሚበርዝ ዘመን የለም:: የዘመን ገዢ የሰው ልጅ ነው:: አንተ እንደምትለው 21ኛው ክፍለ ዘመን የግለኝነት ዘመን ሆኖ ሳይሆን ለዘመኑ እኛ ምቹ ሆነን ስለተገኘን ነው የብቻ ዘመን ያደረግነው:: አብሮ መብላት አብሮ መሆን ነው:: አብሮ መብላት ወንድማማችነት ነው:: ዛሬ ላይ በብዙ ነገራችን ተለያይተን የቆምነው የድሮ መልካም ባህሎቻችንን ስለተውን ነው:: በዘመን ውስጥ መብቀል እንዲህ አይደለም፣ ስልጣኔ የአባቶችን ስርዐት መተው አይደለም..ስልጣኔ ራስን ለዘመን ማዘጋጀት ሳይሆን ዘመንን ለራስ ማዘጋጀት ነው:: አንተ እኔን አባትህን ጎንህ አስቀምጠህ ከሞባይልህ ጋር የምትጫወተው ጊዜን ስለበለጥከው ሳይሆን በጊዜ ስለተበለጥክ ነው:: ሰው በዘመን ሲበለጥ እንዳንተ ነው የሚሆነው:: ከመጣሁ ጀምሮ አንዴም አላየህኝም:: ይሄን ሁሉ ወሬ ሳወራህ እንኳን ቀና ብለህ ቀይ ልሁን ጥቁር አላስተዋልከኝም:: እንብላን ብታውቅ ታየኝ ነበር› ሲሉ ተናግረው ዝም አሉ::

ወጣቱ አሁን አያቸው....የተቀየመ ያዘነ ሽማግሌ ፊት ተጋረጠበት::

‹በአዛውንቶች ልብ ውስጥ ያለችውን ጥንታዊቷን ኢትዮጵያ ፈልጋት:: እርሷን ስታውቅ አሁንህን ትጠላዋለህ.. ድሮነት ምን ያክል ዋጋ እንዳለው ትረዳለህ:: እርሷ ለእኔም ለአንተም ለሁላችንም የጋራ እውነት ናት:: ሲሉ ተናግረው እጃቸውን ወደ ምግቡ ዘረጉ::

መጽሀፌን ዘግቼ ከራሴ ጋራ ግብ ግብ ገጠምኩ:: የሽማግሌው እውነት ውሰጤ ዘልቆ ተሰማኝ:: ከተናገሩት ውስጥ አንድም ውሸት የለም:: እውነት በዛ ቀን ላይ እዛ ቦታ ከእሳቸው ጎን በመቀመጤ ደስ አለኝ:: ኢትዮጵያን እንካ ብለው የሰጡኝ ነበር የመሰለኝ...ደግሞም ሰጥተውኝ:: እንደሳቸው እውነት የነገረኝ ሰው የለም:: በዙሪያዬ ያሉ ብዙ ሰዎች የውሸት ተረት እየፈጠሩ ኢትዮጵያዊነትን የሚያረክሱና የሚያቆሽሹ እንደሆኑ አውቃለው እርሳቸው ግን ልዩ ነበሩ:: በተቀመጥኩበት ራሴን እንዲህ አልኩት... አንተ እኮ ራስክን ብታውቅ፣ ኢትዮጵያዊነት ምን እንደሆነ ብትረዳ የአለም አይኖች ማረፊያ ነበርክ:: በታላቅ ሀይል ተሞልቼ ከወንበሬ ተነሳሁ...ስነሳ ከእንግዲህ በአዛውንቶች ልብ ውስጥ ያለችውን እውነተኛይቱን ኢትዮጵያ ፈልጌ ላገኝ ለራሴ ቃል በመግባት ነበር::

# ዓለም አቀፍ

## የአውሮፓ ህብረት ከሩሲያ የሚያገኘውን ጋዝ ለመተካት ቢያንስ ሶስት ዓመታት እንደሚያስፈልገው ተገለጸ



የአውሮፓ ህብረት ከሩሲያ የሚያገኘውን ጋዝ ለመተካት ቢያንስ ሶስት አመታት ያስፈልገዋል ሲል ዓለም አቀፉ ደረጃ አውጪ ኤጀንሲ አስታውቋል፡፡ ሞስኮ አቅርቦቷን ካቋረጠች ስሎቫኪያ፣ ሃንጋሪ እና ቼክ ሪፐብሊክ በጋዝ እጦት ሳቢያ በጣም ይጎዳሉ ሲል ኤጀንሲው ገልጿል።

የጋዝ አቅርቦቱ በድንገት መቋረጥ የኤጀንሲው መሰረታዊ ጉዳይ አይደለም ሲልም አስገንዝቧል። አሁን ላይ ቡልጋሪያ እና ፖላንድ የጋዝ አቅርቦቱ የተቋረጠባቸው ሲሆን፥ የሌሎች የህብረቱ አባል ሀገራት አቅርቦት መቀነሱንም ኤጀንሲው አስታውቋል።

የጋዝ አቅርቦቱ መቋረጥ ከሚያስከትለው ማህበራዊ ጫና ባለፈ፥ በሀገራቱ ላይ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጫና እና ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት ያስከትላልም ብሏል። ባለፈው ሚያዝያ ወር ሩሲያ ጋዝ መግዛት የሚፈልጉ ሀገራት በሩሲያ መገበያያ ገንዘብ ክፍያ እንዲፈጽሙ መጠየቋ ይታወሳል።

ይህንተከትሎሀገራትይህንየሩሲያትዕዛዝአንፈጽምም በማለታቸው ሩሲያ የጋዝ አቅርቦቷን ማቋረጧና ለተወሰኑ ሀገራትም መቀነሷ ይታወሳል። በያዝነው ወር መጀመሪያ አካባቢም ለጀርመን የምታቀርበውን የጋዝ ምርት “በቴክኒካዊ ችግር ምክንያት” በሚል በ60 በመቶ መቀነሷን አር ቲ በዘገባው አስታውሷል።

## ታዋቂው ሙዚቀኛ አርኬሊ ለዓመታት በፈጸመው ወሲባዊ ጥቃት የ30 ዓመት እስር ተፈረደበት

ታዋቂው አሜሪካዊ ሙዚቀኛ አርኬሊ ታዋቂነቱን በመጠቀም ታዳጊዎችና ሴቶች ላይ ለዓመታት በፈጸመው ወሲባዊ ጥቃት የ30 ዓመት እስር ተፈርዶበታል።አርኤንድ ቢ በተሰኘው የሙዚቃ ስልት ከፍተኛ የዝና ማማ ላይ መውጣት የቻለው የ55 ዓመቱ ሙዚቀኛ መስከረም ወር ላይ ነበር በወሲብ ዝውውር ወንጀልና በማጭበርበር የተከሰሰው።

ለበርካታ ዓመታት ያህል በርካታ ውንጀላዎችን ቢያስተናግድም “ለሰዎች ሰቆቃ ምንም አይነት ሃዘኔታ አላሳየም ግድየለሽም ነበር” ሲሉ ዳኛው ረቡዕ ዕለት ተናግረዋል።የሮበርስ ሲይልቨስተር ኬሊ ወይም በቅፅል ስሙ አርኬሊ ጠበቆችም በውሳኔው ላይ ይግባኝ እንደሚጠይቁ ተናግረዋል።ብይኑ ከመተላለፉ በፊት በሙዚቀኛው ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶች በአርኬሊ ላይ ለመመስከር ፍርድ ቤት ተገኝተው ነበር።

አንጄላ የተሰኘች አንዲት ሴት አርኬሊን "ፓይድ ፓይፐር" ስትል በመጥራት አዳዲስ ጥቃቶችን በተደጋጋሚ በማድረስ “በክፋት የደረጀ” ስትል ወርፋዋለች። ሌሎች ስማቸው ያልተጠቀሱ ሴቶች ደግሞ መንፈሳቸውን እንደሰበረው መስክረዋል።

“እንዲሰማኝ ባደረግከው ስሜት መሞትን እንድመኝ አድርገኸኛል ብላለች” አንዷ ለፍርድ ቤቱ።የእስር ቤት ካኪ መለዮ እና ጥቁር መነጽር አጥልቆ ችሎት የተገኘው አርኬሊ ለመናገርም ሆነ ብይኑም ሲተላለፍ ምንም አይነት ምላሽ አልሰጠም።


የአሜሪካ ዳኛ አን ዶኔሊ ሙዚቀኛው ወሲብን እንደ መሳሪያ በመጠቀም ተጠቂዎች ሊናገሩት የማይችሉትን አጸያፊ ነገሮችን እንዲፈፅሙ አስገድዷቸዋል ብለዋል። አንዳንዶቹም ላይ በወሲብ የሚተላለፉ በሽታዎች እንዲይዛቸው ምክንያት ሆኗል ብለዋል።"ፍቅር ባርነት እና ሁከት መሆኑን አስተምሯቸዋል" ብለዋል ዳኛዋ።

ፍርድ ቤቱ አርኬሊ የሚታወቅባቸውን እንደ ‘አይ ቢሊቭ አይ ካን ፍላይ’፣ ‘ኢግኒሽን’ በመሳሰሉ ተወዳጅ ሙዚቃዎቹ ያተረፈውን ተፅእኖ በመጠቀም ለሁለት አስርት ዓመታት ያህል ታዳጊዎችንና ሴቶች ላይ ወሲባዊ ጥቃት ለመፈጸም እንደ መስህብ ተጠቅሞበታል ብሏል።ስድስት ሳምንታት በወሰደው የብሩክሊን የፍርድ ሂደት ሙዚቀኛው በተለያዩ የአሜሪካ ግዛቶች ሴቶችን እንዴት ያዘዋውር እንደነበር ሰምቷል።

ይህንንም ለማከናወን የሙዚቀኛው ሥራ አስኪያጆች፣ ጠባቂዎችና ሌሎች አጃቢዎች አግዘውታል ተብሏል። በተጨማሪም በአውሮፓውያኑ 1994 አርኬሊ የ15 ዓመት ታዳጊ የነበረችውን ዘፋኝ አሊያህን ለማግባት በሕገ ወጥ መንገድ ዕድሜዋን የሚያጭበረብር ሰነድ ማውጣቷም ተነግሯል።ዘፋኟ አርኬሊን ካገባች ከሰባት ዓመታት በኋላ በአውሮፕላን አደጋ ህይወቷ ማለፉን ቢቢሲ ዘግቧል።



# ስፖርት



## ታላቁ የአፍሪካ ሩጫ በመጪው ጥቅምት በዋሽንግተን ዲሲ ይካሄዳል

ብርሃን ፈይሳ

በአሜሪካዋ ዋሽንግተን ዲሲ ከተማ የሚካሄደው ታላቁ የአፍሪካ ሩጫ በመጪው ጥቅምት ወር ለአራተኛ ጊዜ እንደሚካሄድ ተገለጸ፡፡ በውድድሩ ላይ ከ20 በላይ ታዋቂ ኢትዮጵያውያን አሊምፒያኖችና የዓለም ቻምፒዮኖች እንዲሁም የአገር ባለውለታዎች ተሳታፊ እንደሚሆኑ አዘጋጆቹ አሳውቀዋል፡፡

አሜሪካ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን አዘጋጅነት የሚካሄደውና ባለፉት አራት ዓመታት ፈጣን እድገት እያሳየ በመጣው ታላቁ የአፍሪካ ሩጫ ዘንድሮም ለአራተኛ ጊዜ ሲካሄድ በርካታ ኢትዮጵያውያን እና አፍሪካዊያን ይሳተፋሉ፡፡ «አብሮነት መሻል ነው» በሚል መሪ ሃሳብም ውድድሩ እንደሚካሄድ አዘጋጆቹ አስታውቀዋል፡፡ ሩጫው ከስፖርታዊ ውድድርነቱ ባለፈ ኢትዮጵያውያንን ማሰባሰብ፣ለዳያስፖራው ማህበረሰብ ልጆችን ከባህላቸው ጋር የበለጠ ማቀራረብ እንዲሁም ለተለያዩ በጎ አድራጎት ስራዎች ገቢ ማሰባሰብን ዓላማው አድርጓል። በ5 ኪሎ ሜትሩ ሩጫ ላይ ከአትሌቶች ባለፈ የዳያስፖራው ማህበረሰብ ተካፋይ ሲሆን፤ ምዝገባውም ከዛሬ ጀምሮ በድረገጽ የሚካሄድ ይሆናል፡፡

በዚህ ዝግጅት ከ20 በላይ ታዋቂ ኢትዮጵያውያን ኦሊምፒያኖችና የዓለም ቻምፒዮኖች እንዲሁም የአገር ባለውለታዎች ተሳታፊ እንደሚሆኑም የገለፁት የውድድሩ አዘጋጆች፣ ባለፉት ሶስት መርሃ ግብሮች ላይ የኢትዮጵያ ብርቅዬ አትሌቶች ደራርቱ ቱሉ፣ ቀነኒሳ በቀለ፣ የዲባባ ቤተሰብ፣ ሚሊዮን ወልዴ፣ ፋጡማ ሮባ፣ ብርሃኔ አደሬ፣ ስለሺ ስህን፣ ቁጥሬ ዱለቻ እና ሌሎችም በክብር እንግድነት መገኘታቸውን አስታውሰዋል፡፡




ባለፉት አራት ዓመታት ፈጣን እድገት እያሳየ በመጣው ታላቁ የአፍሪካ ሩጫ ዘንድሮም ለአራተኛ ጊዜ ሲካሄድ በርካታ ኢትዮጵያውያን እና አፍሪካዊያን ይሳተፋሉ፣

በሺዎች ከሚቆጠሩ የዲያስፖራው ማህበረሰብ አባላት ባሻገር ታዋቂ ሰዎችም ውድድሩን ለማበረታታት እንደሚካፈሉ ታውቋል። ባለፉት ውድድሮች የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌደሬሽን ፕሬዚደንት ኮማንደር ደራርቱ ቱሉ በክብር እንግዳነት መገኘቷ ይታወሳል፡፡ ኮማንደር ደራርቱ ቱሉ ከመጀመሪያው ውድድር ጀምሮ በአካል በመገኘት አዘጋጆቹን ስትደግፍ የቆየች መሆኗን ያስታወሱት አዘጋጆቹ፣ ለታየው እድገት አድናቆቷን እንደገለፀችም ጠቁመዋል፡፡ ኮማንደር ደራርቱ ውድድሩ ባለፉት ስልሳ ዓመታት ኢትዮጵያውያን አትሌቶች የሀገራቸውን መልካም ገጽታ በማስተዋወቅ ረገድ ያደረጉት አስተዋጽኦ ምስጋናና እውቅና የሚያገኙበት መድረክ መሆኑን እንደገለፀችም ጠቁመዋል፡፡

የግራንድ አፍሪካን ረን ዋና አዘጋጅ ዶክተር ጋሻው አብዛ በበኩላቸው፤ ዝግጅቱ ከአንድ ቀን የ5 ኪሎ ሜትር የቤተሰብ ሩጫነት የበለጠ ፋይዳ ያለው መርሀግብር መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በማቀራረብ ረገድ ጉልህ ሚና እንዳለውም አክለዋል። አያይዘውም ከሩጫው ጎን ለጎን የዳያስፖራው ማህበረሰብ ለሚኖሩበት የአሜሪካ ማህበረሰብና ለትውልድ ሀገራቸው ኢትዮጵያ የጎላ አስተዋጾኦ ላደረጉ ሰዎች ሽልማት የሚበረከትበት መድረክ እንደሆም አብራርተዋል።

በሩጫው ላይ በአጋርነት ከሚሰሩ ተቋማት መካከል አንዱ የሆነው የዳሽን ባንክ ሲኒየር የዳያስፖራ ባንኪንግ ስራ አስኪያጅ አቶ ያስቻለው አልማው፤ ባንካቸው የማህበረሰብ ግዴታውን ለመወጣት እንደ ታላቁ የአፍሪካ ሩጫ ያሉ ኢትዮጵያውያንን የሚያሰባስቡ ዝግጅቶችን በቀጣይነት በመደገፍ ለዳያስፖራው ማህበረሰብ ምስጋናውን የሚገልጽበት አጋጣሚ መሆኑን ጠቁመዋል። በተለይ የኢትዮጵያ ብሄራዊ እሴት የሆነውን ሩጫ እንደ እንድ መድረክ በመጠቀም በውጭ የሚኖሩ ወገኖችን ግንኙነት ማጠናከርና የባህል ልውውጥ ማድረግን አበክረው የሚደግፉት መሆኑንም አብራርተዋል፡፡

በዝግጅቱ የሚመዘገቡ እና በዕለቱ ውድድሩን የሚያጠናቅቁ ተመዝጋቢዎች በሙሉ ሽልማት በሚያስገኘው እጣ ላይ የሚካተቱ ሲሆን፣ በውድድሩ ማጠናቀቂያ ላይ የመኪናው እድለኛ የሆነው ተሳተፊ በይፋ መድረኩ ላይ ይገለጻል። የአሌክሳንደሪያ ቶዮታ የሴልስ ማኔጀር አቶ ያሬድ ማንአለብህ፤ አፍሪካውያን በተለይም ኢትዮጵያውያን የአሌክሳንደሪያ ቶዮታ የረጅም ዓመታት ደንበኞች መሆናቸውን ገልጸዋል። ይህንንም ደጋግመው ያሳዩ ሲሆን፤ ለእምነታቸው እና የአሌክሳንደሪያ ቶዮታ ቤተሰብ በመሆናቸው በታላቁ የአፍሪካ ሩጫ በኩል ለማመስገን መርጠዋል። በተለይ ዝግጅቱ ማህበረሰብን በማሰባሰብ እና በማወደስ ረገድ ባለፉት ዓመታት ያከናወናቸው ስራዎች «ቅድሚያ ለማህበረሰብ» ከሚለው መርህ ጋር የሚጣጣም በመሆኑ በቀጣይነትም እንደሚደግፉት ጠቁመዋል። አይይዘውም ዝግጅቱ በማህበረሰቡ የተለየ ቦታ የሚሰጠውን የአትሌቲክስ ስፖርት በመጠቀም አብሮነትን ማጎልበት የሚያስችል መሆኑን ገልጸዋል።

**ከከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየአስራ አምስት ቀን የሚታተም**

## የችግኝ ተከላ እና የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት ስራዎች

በሀገራችን የከተሞች ህዝብ ብዛት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ በመምጣቱ ምክንያት የአካባቢ ሙቀት መጨመር፣ የተፈጥሮ ሀብት መመናመን እና የአካባቢ መራቆትን በማስከተሉ የአካባቢን ውበትና ፅዳት ችላ ማለት ከፍተኛ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ምስቅልቅል ከማስከተሉም ባሻገር የከተማን ብሎም የሀገርን ገፅታ በእጅጉ ያበላሻል፡፡

ሀገራችን ዘላቂ የአረንጓዴ ልማት ለመተግበር የተለያዩ ችግሮች እየገጠሟት እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ከእነዚህ ችግሮች መካከል ከፍተኛ የደን መጨፍጨፍ፣ የሕዝብ ቁጥር መጨመር፣ የወንዞች ስነ-ምህዳር መበከል፣ የደረቅና የፍሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ክፍተት፣ በከተማ ፕላን ለአረንጓዴ ልማት የተመላከቱ ቦታዎች ለታለመላቸው ዓላማ አለመዋል (የፕላን ጥሰት)፤ ለአረንጓዴ ልማት የተመላከቱ ቦታዎች የይዞታ ካርታ ማረጋገጫ አለማዘጋጀት እና ሌሎች ተግዳሮቶች በከተሞች ይጠቀሳሉ፡፡

እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ የተለያዩ ጥረቶች የሚደረጉ ቢሆንም ችግሩ እየተከሰተበት ካለው ፍጥነት ጋር ሲነጻጸር ተስፋ የሚሰጥ ሆኖ አይታይም፡፡ በከተሞች የአረንጓዴ ልማት ሥራን ተግባራዊ ለማድረግ ግልጽ የሆኑ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ መመሪያዎችና ስታንዳርዶች የተዘጋጁ ቢሆንም ወደ ተግባር ተለውጠው ውጤት እንዲያመጡ የማድረግ ሥራው ትልቅ ክፍተት ይታይበታል፡፡

በከተሞች የአረንጓዴ ልማት ሥፍራዎችን ለማልማትና ለመንከባከብ የሚደረገው እንቅስቃሴ ከከተማ ከተማ የሚለያይ ቢሆንም አፈጻጸሙ ዝቅተኛ ነው፡፡ ለአረንጓዴ መሰረተ-ልማት የሚከለሉ ቦታዎች በህገ-ወጥ መንገድ ላልተፈለገ ዓላማ የሚውሉበት ሁኔታ በከተሞች ይስተዋላል፡፡ በከተማ ፕላን ስትራቴጂ የተቀመጠውን የ30-30-40 የከተማ መሬት አጠቃቀም መርህን ለመተግበር የተደረገው ጥረትና የተገኘው ውጤትም አናሳ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

በሌላ በኩል የአረንጓዴ ልማት ሥራውን ለማፋጠን ተብሎ በክረምት ወቅት በዘመቻ በሕብረተሰቡና በበጎ ፈቃደኞች የሚሰሩ ሥራዎች በቂ ግንዛቤና የእኔነት ስሜት ሳይፈጠር የሚሰሩ በመሆናቸው በዚህ መልክ በዘመቻ የሚተከሉ ችግኞች ዘላቂ የሆነ እንክብካቤ ስለማይደረግላቸው የአንድ ወቅት ሥራ ብቻ ሆነው የሚቀረቡት ሁኔታ ይታያል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያየዘ ከተሞች የአረንጓዴ ልማት ሥራዎችን ለማሳደግ በሚያስችል ደረጃ የችግኝ ጣቢያዎችን እና ለከተማ ውብት የሚያስፈልጉ የዕጽዋት ዝርያዎችን ከማዘጋጀት አንጻር ብርቱ ጥረት ሲያደርጉ አይታዩም፡፡

ከዚህ አንጻር የሁሉንም ዜጎችና ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ በማረጋገጥ ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ በሀገር አቀፍ ደረጃ እየተከናወነ ያለውን የአረንጓዴ አሻራ ፕሮጀክትን በተቀናጀና በተደራጀ መልኩ በኢትዮጵያ ከተሞች ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመተግበር ጥረት መደረጉ ይታወሳል፡፡ ስለሆነም በ2014 ዓ.ም በሀገር አቀፍ ደረጃ የስድስት ቢሊዮን ችግኝ ተከላ መርሃ-ግብር በከተሞች የአረንጓዴ ልማት ሥራን በማሳደግ ከተሞች ውብ፣ ለቱሪስት ሳቢና ማራኪ፣ ለነዋሪዎቻቸው ምቹ በመሆን የአየር ንብረት ለውጥን እንዲቋቋሙ ትልቅ ድርሻ ያበረክታል፡፡

በተጨማሪም ከአረንጓዴ አሻራ ልማት ጎን ለጎን የአቅመ ደካሞችን መኖሪያ ቤት በማደስ ያለባቸውን ማህበራዊ ችግር ለማቃለል፣ የከተሞች ዋና ዋና መንገዶችን፣ የተዘጉ ቦዮችን እና ጉዳት የደረሰባቸውን የከተማ ተፋሰሶች ለማልማትና ኢኮኖሚያዊ ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች በትምህርት ቁሳቁስ በመደገፍ የከተሞችን የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎትን ባህል ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ የአረንጓዴ ልማትና ውበት ችግርን በዘላቂነት ለመቅረፍ እንዲቻል አገራችን በዘርፉ ስትራቴጂዎችን፣ ስታንዳርዶችን እና ፕሮግራሞችን በመንደፍ በመረባረብ ላይ የምትገኝ ሲሆን ፅዳትና ንፅህናን በተመለከተ በከተሞች ላይ ያለው አዎንታዊ ተፅዕኖ እንደተጠበቀ ሆኖ ለነዋሪዎች ማህበረ-ኢኮኖሚ መሻሻል ያለው ሚና እጅጉን የጎላ ነው፡፡

**የአረንጓዴ መሠረተ ልማት ቦታዎች ለሌላ አገልግሎት ሲውሉ በቸልታ በመመልከት እስካሁን ድረስ በከተሞቻችን ፅዳትና አረንጓዴ ልማት ዘርፍ የሚታዩ መልካም ውጤቶች በታሰበው ደረጃ ሰፍተው መሰረታዊ ለውጥ ማምጣት ባይችሉም ዋናው ግን ሕብረተሰብ አቀፍ እንቅስቃሴ በየደረጃው መካሄድ ባለመቻሉ ነው**

የአረንጓዴ መሠረተ ልማት ቦታዎች ለሌላ አገልግሎት ሲውሉ በቸልታ በመመልከት እስካሁን ድረስ በከተሞቻችን ፅዳትና አረንጓዴ ልማት ዘርፍ የሚታዩ መልካም ውጤቶች በታሰበው ደረጃ ሰፍተው መሰረታዊ ለውጥ ማምጣት ባይችሉም ዋናው ግን ሕብረተሰብ አቀፍ እንቅስቃሴ በየደረጃው መካሄድ ባለመቻሉ ነው፡፡ በአገራችን እየተከሰተ ያለውን የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ ለመቋቋም በአረንጓዴ ልማት ላይ የተመሰረተ ኢኮኖሚን አጠናክሮ ማስቀጠል ለኑሮ ምቹ አካባቢን ለመፍጠር እና ለዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት መሠረት ስለሆነ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖን ለመቋቋም በአረንጓዴ ልማት ላይ የተመሰረተ ኢኮኖሚን አጠናክሮ ማስቀጠል ይገባል፡፡

የአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖው እንዲቀንስ ሕብረተሰቡን በችግኝ ተከላ፣ በአፈር ጥበቃና በውሃ አካላት አያያዝ፣ በመስኖ ልማትና በተፋሰስ ልማት ሥራዎች ላይ እንዲሰማራ በማድረግና ሥራውን በማስቀጠል በተፈጥሮ ላይ የሚከሰቱ ሰው-ሰራሽ ችግሮችን ለመቋቋም የሚያስችሉ ሥራዎችን ለማከናወን አስፈላጊ የግንዛቤ ማስጨበጫ መንገዶችን በመጠቀም ግንዛቤ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡

መንግስት ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች ደረጃ በደረጃ ለመቅረፍ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተለያዩ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች ግቦችና ዕቅዶችን በመቅረጽ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ በዚህም በአረንጓዴ ልማት ዘርፍ የሚታዩ መልካም ጥረቶችን ወደ ላቀ ደረጃ ማሸጋገር እንዲቻል፤ በክረምት ወቅት የችግኝ ተከላ እና የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን በተለያዩ የንቅናቄ መንገዶች ሁሉም የሕብረተሰብ ክፍል ንቁ ተሳትፎ እንዲኖረው ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን በመረዳት እየተሠራ ነው፡፡

ከዚህ አንጻር እንደ ሀገር የታቀደውን የ2014 የክረምት የችግኝ ተከላ መርሃ-ግብር በከተሞች እንዲተገበር፤ የከተማ ነዋሪዎችና የሚመለከታቸው ሁሉ የሚጠበቅባቸውን እንዲወጡ በማስቻል እንደ ሀገር ሊተከል ከታቀደው 6 ቢሊዮን ችግኝ መካከል ከተሞች 196 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ድርሻ አላቸው፡፡ እነዚህ ችግኞች መላውን የከተማ ነዋሪና ባለድርሻ አካላት ባሳተፈ መልኩ ከተተከሉና በቀጣይነት እንክብካቤ ካገኙ ከተሞች ለነዋሪዎቻቸው ምቹ እንዲሆኑ የማስቻል ራዕይን በማሳካት ረገድ ትልቅ ሚና ይኖራቸዋል፡፡

የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር በሀገር አቀፍ ደረጃ በዚህ የክረምት ወቅት ሊተገበር የታቀደውን የችግኝ ተከላ መርሃ-ግብር፣ የአቅመ ደካሞች የቤት እድሳት፣ ለተማሪ የቁሳቁስ ድጋፍ እና የዋና ዋና መንገድ እና የተፋሰስ ጽዳት ሥራ በከተሞች ላይ ተግባራዊ እንዲሆን ለማስቻል ሴክተር ተቋማትን፣ ከተሞችንና ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር ወደ ተግባር ለመግባት እንዲቻል በሚዲያ የታጀበ ሥራን በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

የዚህ ጽሁፍ መዘጋጀትም ሀገራዊ ንቅናቄን ለመፍጠር የተያዘው ዕቅድ አንድ አካል መሆኑ በሁሉም ዘንድ ታውቆ ሁሉም የሕብረተሰብ ክፍል በተለይ ደግሞ የከተማ ነዋሪው ሕብረተሰብ ለጉዳዩ የተለየ ትኩረት በመስጠት ለተግባራዊ ምላሹ ርብርብ እንዲያደርግ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን፡፡